“የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ-መንግስት

ማዕከላዊ ነጋሪት ጋዜጣ

CENTRAL NEGARIT GAZETA

OF THE CENTERAL ETHIOPIA’S REGIONAL STATE

----------ዓመት ቁጥር

ነሐሴ ----------

y¥:k§ê Eኢትዮጵያ ክልል መንግስት

የህዝብ ተወካዮች **M**ክር**b@T -**

ÆqEEnT ywጣ አዋጅ

የወጣ አዋጅ

------**th**Year No -----

August, ----------

/2023

U አዋጅ

አዋጅ ቁጥር 197/2015

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ሕገመንግስትሥራ ላይ መዋሉን ለማሳወቅ የወጣ አዋጅ

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስትን የመሰረቱት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በተወካዮቻቸው አማካይነት ነሐሴ 12 ቀን 2015 ዓ.ም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ሕገ መንግስት ያፀደቁ በመሆኑ የሚከተለው ታውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “ የ 2015 ዓ.ም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 197/2015” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ሕገ መንግስቱ በሥራ ላይ ስለመዋሉ

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ሕገ መንግስት ከነሐሴ ------ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ ውሏል።

3. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ከታወጀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሆሳዕና ፣ነሐሴ----- ቀን 2015 ዓ.ም

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር

መግቢያ

እኛ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የምንገኝ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች፡-

በጋራ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ ተመስርተን በመሰረትነው ክልል ዉስጥ ፍትሃዊ የኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ተጠቃሚነትንና ዕድገትን ለማረጋገጥ፣ በምንመሰርተው ክልል ውስጥ የጋራና የየራሳችን የሆኑ የባህል፣ የቋንቋ፣ የታሪክና የማንነት፣ እሴቶችና ጥቅሞች ያሉን፣ በተለያዩ የግንኙነት ደረጃዎች የተሳሰርን መሆኑን ስለምናምንና ማንነታችን ተከብሮ ያሉን የባህሎችና የቋንቋዎች መከበርንና የማሳደግ መብታችንን ለማረጋገጥ፣ የእምነት እና የህይማኖት እኩልነትና ነፃነትን ለማስፈን እንዲቻል፣

በጋራ የመልማትና የማደግ ፍላጎት ያለንና በሥነ ልቦና አንድነት እና በመልከዓ ምድር የተሳሰርን በመሆናችን ያለንን የሰውና የተፈጥሮ ሀብት ተጠቅመን በጋራ በፍትህዊነትና በእኩልነት፣እንዲሁም ርትዕን መሰረት ያደረገ ተጠቃሚትን ለማረጋገጥ በክልላዊ አደረጃጀት እዉን ማድረግና ማፅናት አስፈላጊ መሆኑን በማመን፣

በክልላችን ብሎም በሀገራችን የብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች አንድነትንና መተማመንን ለማጎልበት እንዲሁም የሀገራችንን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን ለማፅናት፣ ለማስከበርና ለመጠበቅ የወሰንን በመሆኑ፤ እንዲሁም መሰረታዊ የግለሰብና የቡድን ሰብዓዊ መብቶችንና ነጻነቶችን በክልላችን ውስጥ ለማስከበር፣ለማክበርና ለሚሚላት እንዲቻል፤በጋራ ያዳበርናቸውና ያፈራናቸው የመከባበር፣የብዝሀነትና የአብሮነት እሴቶችን ተጠቅመን በክልላችን ሁለንተናዊ እድገትን፣መልካም አስተዳደርን፣ዴሞክራሲንና ሰላምን በዘላቂነት ለማረጋገጥ እንዲቻል በክልላዊ አደረጃጀት መደገፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ዉስጥ አብረውን የነበሩ የሲዳማ ብሔር፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች እና የደቡብ ኢትየጵያ ህዝቦች የራሳቸዉንክልል ለመመስረት ባላቸዉ ህገ መንግስታዊ መብት በመጠቀም በህዝበ ዉሳኔ በክልል የመደራጀት መብታቸውን ያረጋገጡ በመሆኑ፣

የቀረው የክልል አደረጃጀት አስቀድሞ ከነበረው የክልሉ ስያሜ፣ከአስተዳደራዊ ወሰን፣ ርዕሰ ከተማ፣ ዓርማና ሰንደቅ ዓላማ፣ ከመልከዓ ምድራዊ አሰፋፈር እና ሌሎች መሰረታዊ ጉዳዮች አንፃር መሰረታዊ ለዉጦች የተከሰቱ በመሆኑ፣ከእነዚህ ለውጦች አንጻር በመቃኘት ለማጣጣምና ለማስተካከል እንዲቻል የተሻሻለውን የ 1994 ዓ.ም የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሕገ-መንግስትን እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት ዉሳኔ ያስተላለፈ በመሆኑ፣

ከዚህ በላይ ለገለጽናቸዉ ዓላማዎችና እምነቶች ማሰሪያ እንዲሆን ይህንን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ሕገ መንግስት በተወካዮቻችን አማካኝነት አጽድቀናል።

ምዕራፍአንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1. የክልሉ መንግስት መቋቋም እና ስያሜ

በዚህ ህገ መንግስት ዴሞክራሲያዊ አወቃቀር ስርዓትን የሚከተል " የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት " ተብሎ የሚጠራ መንግስት ተቋቁሟል።

አንቀጽ 2. የክልሉ አስተዳደር ወሰን

1. የክልሉ አስተዳደር ወሰን በክልሉ የሚገኙ የዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የአስተዳደር መዋቅሮች ከሌሎች ጎረቤት ክልሎች ካር ያላቸዉ ወሰን ነው።

2. በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉና በአዋሳኝ ክልሎች መካከል የወሰን አከላለል ለውጥን በተመለከተ በፌዴራሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 48 እና አንቀጽ 62 (6) መሰረት የሚወሰን ይሆናል።

አንቀጽ 3. የክልሉ ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ

1. የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የራሱ ሰንደቅ ዓላማና ኦፊሴላዊ ዓርማ ይኖረዋል፤

2. ሰንደቅ ዓላማው ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሐል ነጭ ፣ከታች ቀይ ሆኖ በመሐሉ ክልላዊ ዓርማ ይኖረዋል፤ ሦስቱም ቀለማት እኩል ሆነው በአግድም ይቀመጣሉ፤ ዝርዝሩ የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ህግ ይወሰናል፤

3. በሰንደቅ ዓላማው ነጭ ቀለም መደብ መሀል ላይ በክብ ቅርጽ እኩል መጠን ያላቸው አስር ሰማያዊ ኮከቦች የሚቀመጡ ይሆናል፤

4. በንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ የተጠቀሱት አስሩ ኮከቦች ክልሉን የመሰረቱትን አስሩን ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦችን የሚወክሉ ሆነው እኩልነታቸውንና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንጸባርቅ ይሆናል፤

5. የክልሉ ኢፊሴላዊ አርማ ክብ ሆኖ ከላይ ቀጥታና እኩል ከሆኑ መስመሮች የተዋቀረ አንድ ሰማያዊ ኮከብ፣በግራ በኩል የስንዴ ዘለላ፣በቀኝ በኩል የማሽን ጥርስ፣በመሀሉ ላይ አንድ ጎጆ ቤትና ከጎጆ ቤቱ በስተቀኝ በኩል የእንሰት ተክል እና በስተግራ በኩል የበርበሬ ተክል ከነዛላው ይቀመጣል፤ዝርዝሩ የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 4. የክልሉ መዝሙር

የክልሉ የህዝብ መዝሙር በክልሉ የሚኖሩ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ያላቸውን ጽኑ እምነትና ፍላጎት፣ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነትን፣ የማህበራዊና ቁሳዊ ቅርስ ባለቤትነትን፣ ጀግንነትንና የሰራ ታታሪነትን፣ ለዴሞክራሲ፣ ለሠላም፣ ለፍትህና ለእኩልነት ጸንቶ መቆምን፣ ክልሉ ከሌሎች የሀገሪቱ ህዝቦች ጋር በጋራ ለመኖር ያላቸውን ቁርጠኝነት፣ በክልሉ የሚኖሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦችን የጋራ ታሪክ፣ ወግ፣ እሴትና ባህል ማበልጸግን የሚያሳይ ብሩህ ተስፋ ሰንቆ በጋራ ተያይዞ መልማትንና ማደግን በሚገልፅ መልኩ ይዘጋጃል፤ ዝርዝሩ የክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 5. ስለ ቋንቋ

1. በክልሉ የሚነገሩ ቋንቋዎች እኩል እውቅና ይኖራቸዋል፤
2. የክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው፤
3. በየደረጃው የሚገኙ ዞኖችና ልዩ ወረዳው በየምክር ቤቶቻቸው የየራሳቸውን የሥራ ቋንቋ ሊወስኑ ይችላሉ።

አንቀጽ 6. ርዕሰ ከተማ

1. የክልሉ መንግስት አንድ ርዕሰ ከተማና ብዝሀ ከተሞች ይኖሩታል፤
2. የክልሉ መንግስት ርዕሰ ከተማ ሆሳዕና ነው፤

3. የክልሉ ብዝሃ ከተሞች ወልቅጤ፣ ወራቤ፣ ዱራሜ ቡታጅራ፣ ቁሊቶ እና ሳጃ ናቸዉ።

4. የክልሉ መንግስት ርዕሰ ከተማ እና ብዝሀ ከተሞች ተጠሪነታቸው ለሚገኙበት የአስተዳደር መዋቅር ይሆናል፤

5. የክልሉ ርዕሰ ከተማ እና የብዝሀ ከተሞች ህጋዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 7. የዶታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

ምዕራፍ ሁለት

የሕገ መንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎች

አንቀጽ 8. የህዝብ ሉአላዊነት

1. የክልሉ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የክልሉ መንግስት የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች ናቸው፤

2. ሉዓላዊነታቸውም የሚገለጸው በዚህ ሕገ መንግስት መሰረት በሚመርጧቸው ተወካዩቻቸው እና በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል።

አንቀጽ 9. የሕገ መንግስት የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፦

1. ይህ ሕገ መንግሥት በክልሉ የበላይ ሕግ ነው። ማንኛውም ሕግ፣ልማድ፣አሰራር፣የመንግሥት አካል ወይም የባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚጋጭ ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፤

2. ማንኛውም በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው፣የመንግሥት አካላት፣የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማህበራትና ተቋማት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ይህንን ሕገ መንግሥት የማክበር፣ የማስከበርና በሕገ መንግሥቱ የመተዳደር ግዴታ አለባቸው፤

3. በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በሌላ መንገድ የክልሉን መንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

አንቀጽ 10. መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች እና ነጻነቶች

1. መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰዉ ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣የማይነጠሉ፤ ሁሉን አቀፍ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው።

2. የግለሰብና የቡድን መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች እና ነፃነቶች እኩል ጥበቃ ያገኛሉ።

አንቀጽ **11.** የመንግስትና የሃይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፣
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም፤
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፤ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

አንቀጽ **12.** የመንግስት አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት

1. የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ፣ ተጠያቂነት ባለው እና ሌሎች የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን በተከተለ መንገድ መከናወን አለበት፤
2. የመንግሥት ባለሥልጣናት እና የሕዝብ ተመራጮች የተሰጣቸውን ኃላፊነት ሲያጓድሉ ተጠያቂ ይሆናሉ፤
3. ሕዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳ ይችላል፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

አንቀጽ **13.** የመንግስት አካላት የሥልጣን ክፍፍል

1. **የክልሉ መንግስት የሥልጣን ክፍፍል በህግ አውጭ፣ በህግ አስፈጻሚ እና በህግ ተርጓሚ አካላት የተደራጀ ይሆናል፤**
2. **የመንግስት አካላት አንዱ በሌላው ሥልጣንና ተግባር ላይ ጣልቃ አይገቡም፤**
3. **በንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም በመንግስት አካላት መካከል በህግ ተለይቶ የተደነገገን የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓትን አያስቀርም።**

አንቀጽ **14.** ነጻና ገለልተኛ የፍትህ አስተዳደር ስርዓት

1. በክልሉ ነፃ እና ገለልተኛ የሆነ የፍትህ አስተዳደር ስርዓት ይኖራል፤
2. የፍትህ አካላት ነፃና ገለልተኛ ሆነው የህዝብን ሠላምና ደህንነት ለማረጋገጥ እና መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶችን ለማስከበር የሚችሉ መሆን አለባቸው፤
3. የፍትህ አስተዳደር አካላት ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ነፃነታቸውንና ገለልተኛነታቸውን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፤
4. ማንኛዉም አካል የፍትህ አስተዳደር አካላትን የተግባር ነጻነትንና ገለልተኛነትን የማክበር ግዴታ አለበት።

ምዕራፍ ሦስት

መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች እና ነጻነቶች

አንቀጽ **15.** የመሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች እና ነጻነቶች አተረጓጎም

የዚህን ህገ መንግስት ድንጋጌዎች ለመተርጎም አለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውንና የተለመዱ የሕገ መንግስት አተረጓጎም መርሆችን ተፈጻሚ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩትን መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶችን እና ነፃነቶችን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት፣ ስምምነቶች፣ ሠነዶችና መርሆዎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ድንጋጌዎችና መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ።

አንቀጽ **16.** የመሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች እና ነጻነቶች አፈጻጸም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልል መንግስት የሕግ አውጪ፣የሕግ አስፈፃሚ እና የዳኝነት አካላት በዚህ ምዕራፍ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበር፣የማስከበር እና የማሟላት ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፤

2. ማንኛውም በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ የንግድ ድርጅት፣ ሌሎች ማህበራትና ተቋማት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ይህንን የመሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች እና ነጻነቶችን የማክበር፣የማስከበርና የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፤

3. በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱት አካላት የመሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች እና ነጻነቶችን አስመልክቶ ያለባቸውን ግዴታ ባለመወጣት ለሚደርስ ጉዳት ካሣን መክፈል ጨምሮ አግባብነት ባላቸው ህግጋት ተጠያቂ ይሆናሉ።

አንቀጽ **17.** የሕይወት መብት

1. ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው፤

2.ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም።

አንቀጽ **18.** የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።

አንቀጽ **19.** የነፃነት መብት

1. በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ነፃነቱን አያጣም፤

2.ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ ሊያዝ፤ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም።

አንቀጽ **20.** ኢ-ሰብአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው፤

2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት አይያዝም፤

3. በማንኛውም ሁኔታና አላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው፤

4. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታ ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሰራ ማድረግ የተከለከለ ነው፤

5. በንዑስ አንቀጽ 4 በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት የሚለው ሀረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም።

ሀ) ማንኛውም የህግ ታራሚ በእስራት ላይ ባለበት ጊዜ በሕግ መሰረት እንዲሰራ የተወሰነውን፣በቀላል እስራት ተፈርዶበት በአማራጭ ቅጣት የጉልበት ሥራ ግዴታ የተጣለበት፣

ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሰራውን ማንኛውንምሥራ፤

ለ) ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ህሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠውን አገልግሎት፤

ሐ) የማህበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውንም አገልግሎት፤

መ) በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈፀመውን ማንኛውንም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት ሥራ።

አንቀጽ 21. የተያዘ ሰው መብት

1. ወንጀል ፈፅሟል በሚል የተያዘ ሰው የተጠረጠረበትን ወይም የተከሰሰበትን ወንጀልና ምክንያቱን በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባው ቋንቋ እንዲነገረው መብት አለው፤
2. የተያዘ ሰው ከተያዘበት ሰዓት ጀምሮ ምርመራ በሚቀጥልበት በማናቸውም ጊዜ ወይም ደረጃ የመረጠውን የህግ ባለሙያ ወይም ጠበቃ የማማከር መብት አለው፤
3. የተያዘ ሰው ያለመናገር መብት አለው፤ ቃሉን ለመስጠት የፈቀደ እንደሆነ የሚሰጠው ማንኛውም ቃል በፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መረዳት በሚችለው ቋንቋ በግልጽ ሊነገረው ይገባል፤
4. የተያዘ ሰው በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው፤ ይህም ጊዜ ሰውዬው ከተያዘበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ምክንያታዊ ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም፤ ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረበ በተጠረጠረበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽለት መብት አለው፤
5. የተያዘ ሰው የያዘው ፖሊስ ወይም የህግ አስከባሪ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አለው፤
6. ፍርድ ቤቱም አመልካቹ የተያዘው ወይም የታሰረው ከህግ ውጭ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ወዲያዉኑ እንዲለቀቅ ወይም ነፃነቱ እንዲረጋገጥ ማዘዝ አለበት፤
7. በንዑስ አንቀጽ ሰባት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘ ሰው የወንጀል ምርመራ ለማጣራት ስልጣን ባለዉ አካል ጥበቃ ስር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግአስከባሪ ባለስልጣኖች ምርመራውን አጣርተዉ የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤትእንዲቀርብ ያለውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት፤
8. የተያዘ ሰው በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምን አይገደድም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፤
9. የተያዘ ሰው በዋስ የመፈታት መብት አለው። ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፤
10. በህግ በልዩ ሁኔታ የሚደነገጉ ህጎች እንደተጠበቁ ሆነውማንኛውም ሰውየውል ግዴታውን ባለማሟላቱ ብቻ አይያዝም፤አይታሰርም።

አንቀጽ 22. የተከሰሰ ሰው መብት

1. የተከሰሰ ሰው ክስ ከቀረበበት በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ለህዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አለው፤
2. ለሕፃናት ልዩ ጥቅምና ደህንነት ሲባል በወንጀል የተከሰሱ ህጻናት የክስ መሰማት ሂደት በዝግ ችሎት መሆን አለበት፤
3. በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተከራካሪዎችን የግል ህይወት፣ የህዝብን ሞራል ወይም የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የክስ መሰማት ሂደት በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፤
4. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገረው፣ ክሱን በጽሁፍ በነፃ የማግኘት እና ማስረጃዎች የሚያስረዱበትን ጉዳይ የማወቅ መብት አለዉ፤
5. በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠርና በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለዉ፤
6. የቀረበበትን ማናቸውም ማስረጃ የመመልከትና የማግኘት፣ የቀረበበትን ምስክር የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችለውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ፣መከላከያ ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙለት የመጠየቅ፣መከላከያ ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ የማግኘት መብት አለው። ሆኖም በዚህ ንኡስ አንቀጽ የተመለከቱት መብቶች የምስክሮችን እና የተጎጂዎችን ደህንነት ለመጠበቅ በሚወጡ ህጎች መሰረት ሊገደቡ ይችላሉ፤
7. በራሱ ወይም በመረጠው የሕግ ጠበቃ አማካኝነት የመከራከር፣ የጠበቃ እርዳታ የማግኘት መብት እንዳለው የማወቅ፣ በራሱ ወጪ ጠበቃ የማቆም አቅም ከሌለው የጥብቅና አገልግሎት በነፃ ከመንግስት የማግኘት መብት አለው፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፤
8. የተከሰሰ ሰው በዋስ የመፈታት መብት አለው፤ ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፤
9. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸዉ ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለዉ። ይግባኝ የሚቀርብበት ፍርድ ቤት የሥራ ቋንቋዉ ፍርዱ ከተሰጠበት ፍርድ ቤት የሥራ ቋንቋ የሚለይ ከሆነ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ተርጉሞመስጠት አለበት፤
10. የፍርድ ቤቱ ክርክር በማይገባው ቋንቋ በሚካሄድበት ሁኔታ በመንግስት ወጪ ክርክሩ እና ማስረጃው እንዲተረጎምለት የመጠየቅ መብት አለዉ።

አንቀጽ 23. በጥበቃ ስር ያሉ እና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት

1. በጥበቃ ስር ያሉ እና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸዉን በሚጠብቅ ሁኔታ የመያዝ መብት አላቸዉ። አያያዛቸዉን በተመለከተ አግባብነት ያላቸዉ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ደንቦች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፤
2. ከትዳር ጓደኞቻቸዉ፣ ከቤተሰቦቻቸውና ከቅርብ ዘመዶቻቸዉ፣ ከህይማኖት አማካሪዎቻቸዉ፣ ከህኪሞቻቸዉ፣ከህግ አማካሪዎቻቸዉ እና ከሰብአዊ መብት ተቋማት ጋር የመገናኘት ወይም ለመጎብኘት መብት አላቸዉ።

አንቀጽ 24. የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛዉም ሰዉ የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በህግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊከሰስ ወይም ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረዉ የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛዉም ሰዉ ላይ አይወሰንም፤

2. ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣዉ ሰዉ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣዉ ህግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

አንቀጽ 25. በአንድ ወንጀል ድጋሚ ክስ እና ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛዉም ሰዉ በወንጀል ህግ እና ሥነ-ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ዉሳኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይምበነፃ በተሰናበተበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

አንቀጽ 26 የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ ሰብዓዊ ክብሩ እና መልካም ስሙ የመጠበቅ መብት አለዉ፤

2. ማንኛዉም ሰዉ የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነጻ የማሳደግ መብት አለዉ፤

3. ማንኛዉም ሰዉ በማንኛዉም ሥፍራ በሰብዓዊነቱ እዉቅና የማግኘት መብት አለዉ።

አንቀጽ 27. የእኩልነት መብት

1. ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸዉ፤ በመካከላቸዉም ማንኛዉም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ እድሜ፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በኃይማኖት፣ በእምነት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣በሀብት፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በትዉልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩል እና ተጨባጭ የሆነ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸዉ፤

2. በንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግስት ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸዉ የማህበረሰብ ክፍሎች ስለሚደረግ ልዩ ድጋፍ በተመለከተ በዝርዝር ህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 28. የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ የግል ህይወቱ፣ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለዉ። ይህ መብት ሰዉነቱ፣ መኖሪያ ቤቱ እና ንብረቱ ከመመርመር ወይም ከመበርበር እንዲሁም በግል ይዞታዉ ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል፤

2. ማንኛዉም ሰዉ በግል የሚፅፋቸው እና የሚግፋቸው፣በፖስታ የሚልካቸዉ ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚያደርጋቸዉ ግንኙነቶች አይደፈሩም፤

3. የመንግስት አካላት ወይም ማንኛውም ሰዉ እነዚህን መብቶች የማክበር እና የማስከበር ግዴታ አለባቸዉ፤

4. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ እና ብሔራዊ ደህንነትን፣ የህዝብን ሠላም፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናን እና የህዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነጻነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሠረቱ ዝርዝር ህጎች መሠረት የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ ይችላል።

አንቀጽ 29. የሃይማኖት፣ የህሊናና የእምነት ነጻነት

1. ማንኛዉም ሰዉ የማሰብ፣ የህሊና፣ የእምነት እና የሃይማኖት ነጻነት አለዉ። ይህ መብት ማንኛዉም ሰዉ የመረጠዉን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንናእምነቱን ለብቻዉ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣የመተግበር፣የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል፤

2. የሃይማኖት ወይም የእምነት ተከታዮች ሃይማኖታቸዉን ወይም እምነታቸውን ለማስፋፋት እና ለማደራጀት የሚያስችሏቸዉን የሃይማኖት ወይም የእምነት የትምህርት እና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ፤

3. ማንኛዉም ሰዉ የሚፈልገዉን ሀይማኖት ወይም እምነት ለመያዝ ያለዉን ነጻነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታበማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም፤

4. ወላጆች እና ህጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸዉ ወይም በሀይማኖታቸው መሠረት የሃይማኖታቸዉን ወይም የእምነታቸውን የመልካም ሥነ- ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸዉን የማሳደግ መብት አላቸዉ፤

5. ሃይማኖትን እና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለዉ የህዝብ ደህንነት፣ሠላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የህዝብን ሞራል ሁኔታ፣የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች፣ ነጻነቶች እና መንግስት ከሃይማኖት ነጻ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ህጎች ይሆናል።

አንቀጽ 30. በሰብዕና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች፣ የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለ ፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር፣ ወይም ኢ-ሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በሕግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምሕረት ወይም በይቅርታ አይታለፉም።

አንቀጽ 31. የአመለካከት እና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል።

2. ማንኛውም ሰው ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል።

3. የፕሬስ፣ ሌሎች መገናኛ ብዙሀን እና የሥነ-ጥበብ ፈጠራ ነጻነት ተረጋግጧል። የፕሬስ ነጻነት በተለይ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ) የቅድሚያ ምርመራ በማንኛዉም መልክ የተከለከለ መሆኑ፤

ለ) ህዝብና መንግስትን የሚመለከት መረጃ የማግኘት መብት፤

4. ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሀሳቦች እና አመለካከቶች በነጻነት መንሸራሸራቸዉን ለማረጋገጥ ሲባል ሚዲያ በተቋምነቱ የአሰራር ነጻነት እና የተለያዩ አስተያየቶችን የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረዉ የህግ ጥበቃ ይደረግለታል፤

5. በክልሉ መንግስት በጀት የሚካሄድ ወይም በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ የመገናኛ ብዝሀነትን የሚያስተናግድ ሆኖ የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለዉ ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል፤

6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸዉ የሚችለዉ የሀሳብ እና መረጃ የማግኘት ነጻነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱ እና ሊያስከትል በሚችለዉ አስተሳሰባዊ ዉጤት ሊገታ አይገባዉም በሚል መርህ ላይ ተመሥርቶ በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል፤

7. የክልሉን ህዝብና ብሔራዊ ደህንነት፣ የሌሎች ሰዎችን መብት፣ ክብር እና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል በእነዚህ መብቶች እና ነጻነቶች ላይ ህጋዊ ገደቦች ሊደነገጉ ይችላሉ፤

8.የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የተከለከሉ ናቸዉ፤

9. ማንኛዉም ሰዉ ከላይ በተጠቀሱት መብቶች እና ነጻነቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ህጋዊ ገደቦችን ጥሶከተገኘ በህግ ተጠያቂ ይሆናል።

አንቀጽ 32. የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ አቤቱታ የማቅረብ ወይም አስቀድሞ በማሳወቅ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ማንኛዉም ዓይነት መሳሪያ ሳይዝ ከሌሎች ጋር በመሆን የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና መብት አለዉ፤

2.ከቤት ዉጪ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚካሄድባቸው ቦታዎች በህዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ሰብአዊ መብቶችን እና ነጻነቶችን፣ የህዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያለው ሥርዓት ሊደነገግ ይችላል፤

3. መንግስት የሰላማዊ ሰልፍ ተሳታፊዎችንና የሌሎች ዜጎችን ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤

4. በዚህ አንቀጽ ስር የተጠቀሱ ሰብዓዊ መብቶች እና ነጻነቶች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ደህንነት፣ የሰዉን ክብርና መልካም ዝና ለመጠበቅ፣ የግጭትና ጦርነት ቅስቀሳዎችን እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ህጎች መሰረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።

አንቀጽ 33. የመደራጀት መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ ለማንኛዉም ህጋዊ ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለዉ፤ ይህምየሠራተኞችን እና የአሰሪዎችን ማህበር መመስረትና አባል የመሆን መብትንም ይጨምራል፤

2. በዚህ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ደህንነት፣የህዝብ አንድነትና ደህንነት፣ ጤና፣ ሞራል እና የሌሎችን መብትና ነጻነት ለመጠበቅ በሚወጣ ህግ ሊገደብ ይችላል።

አንቀጽ 34. የመዘዋወር ነጻነት እና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት መብት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በህጋዊ መንገድ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው በመረጠዉ የክልሉ አካባቢ የመዘዋወር ነጻነት፣ መኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ሰርቶ የመኖር፣ንብረት የማፍራትና የመያዝ፣ያለመፈናቀል፣እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከክልሉ የመውጣትና ተመልሶ የመግባት መብት አለው።

አንቀጽ 35. የግል፣ የጋብቻና የቤተሰብ መብት

1. ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮአዊ መነሻ ነው፤ ከሕብረተሰቡና ከመንግስት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፤

2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ይመሰረታል፤

3. በህግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣በሀይማኖት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግባቸው የመጋባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፤

4. ወንድና ሴት ተጋቢዎች ጋብቻ ሲፈጽሙ፣በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው፤

5. በፍቺ ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች በክልሉ የቤተሰብ ህግ መሰረት ይወሰናል፤

6. **በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም** በሐይማኖት ወይም በባህል ሥርዓት ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና ተሰጥቷቸዋል፤

7. ይህ ሕገ መንግስት የግልና የቤተሰብ ጉዳዮችን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖት ወይም በባህል ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

አንቀጽ 36. የሴቶች መብት

1. ሴቶች እና ወንዶች ይህ ሕገ መንግስት ባረጋገጠላቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ እኩል መብት አላቸው፤

2. ሴቶች በዚህ ህገ መንግስት በተደነገገው መሰረት በጋብቻ ከወንዶች እኩልመብት አላቸው፤

3. ሴቶች በማህበረሰብና በባህል በበታችነትና በልዩነት ሲታዩ በመቆየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን የእኩልነት እና የፍትህ መጓደል ለማረም ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፤

4. በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በመንግስትና በግል ተቋማት ውስጥ ሴቶች በእኩልነትና በፍትሐዊነት ተጠቃሚ፣ ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው፤

5. ሴቶች ከጎጂ ልማድ ተፅዕኖ ለመላቀቅ ያላቸውን መብት መንግስት ማክበርና ማስከበር አለበት፤

6.ሴቶችን የሚጨቁኑ፣ በአካላቸው፣ በአዕምሮአቸው እና በሥነ ልቦናቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች፣ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው፤

7. ሴቶች የቅጥር፣ የእኩል ክፍያ፣የሥራ ዕድገት እና ጡረታን የማግኘትና የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው፤

8. በመንግስት መሥሪያ ቤቶች፣በግል ድርጅቶች ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶች የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፦

ሀ) የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሰራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት፣ የህፃኑንና የቤተሰቧን ደህንነት ከግምት በማስገባት ይሆናል፤

ለ) የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሰረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ ሆኖ የእርግዝና ጊዜ ምርመራ ፈቃድንም ሊጨምር ይችላል፤

ሐ) ለሚያጠቡ እናቶች ለህጻናት እንክብካቤ ሲባል አቅም በፈቀደ መጠን በሚሠሩባቸዉ ሥፍራዎች ምቹ ሁኔታ ይመቻቻል፤

መ) በንዑስ አንቀጽ 8 የተደነገጉ መብቶች አፈጻጸም በህግ ይወሰናል።

9. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርትና መረጃ እና አቅም በፈቀደ መጠን የጤና አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው፤

10. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀም፣ የማስተላለፍ፣ የመውረስና የማውረስ መብት አላቸው፤

11. ሴቶች መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደር፣ በመቆጣጠር፣ በመውረስና በማውረስ ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፤

12. ሴቶች በክልሉ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድ እና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚመለከቱ ፕሮጀክቶች ላይ የመሳተፍ መብት አላቸው፤

13. ሴቶች የፖለቲካ ስልጣንና ተሳትፎ የማግኘት መብት አላቸው።

አንቀጽ 37. የሕፃናት መብት

1. በክልሉ ያለ ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት፦

ሀ) በሕይወት የመኖርና የማደግ፣

ለ) ከሞት ቅጣት የመጠበቅ፣

ሐ) የልደት ምዝገባ፣ስምና ዜግነት የማግኘት፣

መ) ወላጆችን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸው ሰዎችን የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፤

ሠ) ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶችና ሥራዎች የመጠበቅ፣

ረ) በትምህርቱ፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎችን እንዲሰራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመቆጠብ፣

ሰ) ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የመጠበቅ፣

ሸ) በወላጆች፣ በቤተሰብ አባላት፣ በማህበረሰብ፣ በትምህርት ቤቶች፣ በወጣት አጥፊዎች ተሐድሶና ፀባይ ማረሚያ ማዕከል፣በጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ በግል እንክልማውታን፣ በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት በአካል ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው፤

2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በወላጆች፣ በቤተሰብ አባላት፣ በማህበረሰብ፣ በትምህርት ቤቶች፣ በወጣት አጥፊዎች ተሐድሶና ፀባይ ማረሚያ ማዕከል፣ በበጎአድራጎት ድርጅቶች፣ በግል እንክልማውታን፣ በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣናት እና በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ልዩ ጥቅምና ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት፤

3. ማንኛውም ሕፃን በሚመለከተው ጉዳይ ሁሉ ሀሳቡን በነፃነት የመግለፅ መብት አለው፤

4. ሕፃኑ የሚያቀርበው ሀሳብ በእድሜውና በአዕምሮ የመብሰል ሁኔታው እየታየ ተገቢው ክብደት ይሰጠዋል፤

5. በንዑስ አንቀጽ 4 ለተደነገገው ዓላማ ሲባል ሕፃኑን የሚመለከት ጉዳይ በዳኝነት ወይም በአስተዳደር አካል በሚታይበት ጊዜ ራሱ በቀጥታ፣ በሞግዚቱ ወይም ህጻኑን ለመወከል አግባብ ባለው አካል በኩል የመሰማት መብት አለው፤

6. ሕጻናት እና ወጣት አጥፊዎች በተሐድሶ ማዕከልና ጸባይ ማረሚያ ተቋማት የሚገኙ፣ በመንግስት ድጋፍ የሚያድጉ ወጣቶች፣በመንግስት ወይም በግል እንክልማውታን ወይም በጎ አድራጎት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው፤

7. ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ውስጥ ከተወለዱ ሕፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው፤

8. መንግስት ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፤ በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ስርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል።

አንቀጽ 38. ፍትህ የማግኘት መብት

1.ማንኛዉም ሰዉ በዳኝነት ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብ፣ያለ አድሎ በእኩልነት የመሰማት እና ፈጣን ዉሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለዉ፤

2. በንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉን ዉሳኔ ወይም ፍርድ፡-

ሀ) ማንኛዉም ማህበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣

ለ) ማንኛዉንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸዉን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይንም የቡድን አባል የመጠየቅ እና የማግኘት መብት አለዉ።

አንቀጽ 39. የመምረጥ እና የመመረጥ መብት

1. ማንኛውም በክልሉ ነዋሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ምርጫ ህግ በተደነገገዉ የመምረጥና የመመረጥ ዕድሜ መሠረት በቀለም፣ በዘር፣ በአካል ጉዳት፣በጾታ፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በኃይማኖት፣ በእምነት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከትና አቋም ላይ የተመሠረተ ልዩነት ሳይደረግበት፡-

ሀ) በቀጥታ ወይም በተወካዮቹ አማካይነት በህዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣

ለ) በየጊዜዉ በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥ እና የመመረጥ መብት አለው።

2. በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሠሪዎች እና በሙያ ማህበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀዉን ጠቅላላ እና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማንኛዉም ሰዉ በፍላጎቱ አባል የመሆን፣ የመምረጥ እና የመመረጥ መብት አለው፣

3. በዚህ ንኡስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ድርጅቶች ዉስጥ ለኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነጻ እና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መፈጸም አለባቸው፣

4. በንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው ቢኖርም የመምረጥና የመመረጥ መብቶች ከጠቅላላ ሀገራዊ የምርጫ ህግና የምርጫ አስፈጻሚ ተቋም ከሚያወጣቸው ዝርዝር ህግጋት ጋር በተጣጣመ መልኩ መተርጎም አለባቸው፣

5. የንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌዎች የህዝብን ጥቅም የሚነኩ ከሆነ በህዝባዊ ድርጅቶች ላይም ተፈጻሚነት አላቸው።

አንቀጽ 40. የክልሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መብት

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የክልሉ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር እና የራሳቸውን ክልል የመመስረት መብታቸው የተጠበቀ ነዉ፤

2. ማንኛውም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በሰፈሩበት መልክዓ ምድር ራስን በራስ የሚያስተዳድሩባቸውን መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በአስተዳደር መዋቅሮች፣ በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ተመጣጣኝ፣ ሚዛናዊና ፍትሀዊ ውክልና የማግኘት መብት አላቸው፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤

3. ማንኛዉም የክልሉ ብሔር፣ ብሔረሰብ እና ህዝብ በቋንቋዉ የመናገር፤ የመማር የመጻፍ፣ የመዳኘት፣ ቋንቋዉን የማሳደግ፣ ባህሉን የመግለጽ፤ የማዳበር፣ የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለዉ፤

4. የክልሉ መንግስት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የአፍ መፍቻ ቋንቋ በእኩልነት እንዲያድግ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

5. የክልሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በዚህ ህገ መንግስት በተቀመጡ መብቶች እኩል ተጠቃሚ ናቸው፤

6. በዚህ ሕገ መንግስት ዉስጥ “ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ህዝብ” ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸውን ባህርይ የሚያሳይ ማኅበረሰብ ነው። ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባሕል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው።

አንቀጽ 41. የንብረት መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ የግልና የጋራ ንብረት የማፍራት እና ባለቤት የመሆን መብት አለው፤

2. በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው መብት የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በህግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማዉረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብትን ያካትታል፤

3. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ሲባል “የግል ንብረት” ማለት ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣ህጋዊ ሰዉነት ያላቸው ኢትዮጵያዊ ማህበራት ወይም በህግ በተለየ ሁኔታ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸዉ ማኅበረሰቦች

በጉልበታቸዉ፣ በመፍጠር ችሎታቸዉ ወይም በካፒታላቸዉ ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረዉ ዋጋ ያለዉ ዉጤት እንዲሁም በህግ አግባብ መሬትን የመያዝና የመጠቀም መብትን ይጨምራል፤

4. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነዉ፤ መሬት የማይሸጥና የማይለወጥ የክልሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ፤

5. የክልሉ አርሶ አደሮች ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነጻ የማግኘት፣ የመጠቀምና በህግ አግባብ ካልሆነ በስተቀር ከይዞታቸው ያለመነቀል መብት አላቸው፤

6. ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በክልሉ ለመኖሪያ ቤት እና ለንግድ ሥራ መሬት የማግኘት መብት አለው፣በህግ አግባብ ካልሆነ በስተቀር ከይዞታው ያለመነቀል መብት አለው፤ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፤

7. ማንኛውም ሰው ለኢንቨስትመንት ዓላማ መሬት የማግኘት መብት አለው፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤

8. በንዑስ አንቀጽ 5፣6 እና 7 የተደነገገው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የገጠር እና የከተማ መሬት አስተዳደር፣ አያያዝና አጠቃቀም አግባብ ባለው ህግ መሠረት ይወሰናል፤

9. በክልሉ ነዋሪ የሆነ ማንኛውም ኢትዮጲያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ቋሚ ንብረት የማፍራት፣የመገንባት እና ማሻሻያ የማድረግ መብት አለዉ፤

10. በንዑስ አንቀጽ 9 የተደነገገው መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማዉረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማስተላለፍ እና የካሳ ክፍያ የማግኘት መብትን ያካትታል፣

11. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ለሕዝብ የተሻለ ጥቅምና ዕድገት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ለግል ባለንብረቱ በንዑስ አንቀጽ 9 እና 10 በተመለከተው አግባብ መብቱን በመጠበቅ ንብረቱን ለመዉሰድ ወይም ለመገልገል ይችላል፣

12. በንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት የሚወሰደው እርምጃ በአንድ አካባቢ ልማዳዊ አኗኗር ዘይቤን ተከትሎ የሚኖሩ ዜጎች የኑሮ ዘዬ እንዲቀይሩ በማያስገድድ መልኩ መሆን አለበት፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

13. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉውስጥ በመንግስት ወይም በግል በሚካሄዱ የልማት ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸዉ የተነካባቸዉ ሰዎች፡-

ሀ/ በጊዜያዊነት በቂ እርዳታና ድጋፍ የማግኘት፣

ለ/ ዘላቂታ ወዳለው ምቹ የመኖሪያ አካባቢ የመዛወር፣

ሐ/ ተመጣጣኝ የገንዘብ ካሣ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸዉ።

አንቀጽ 42. የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች

1. ማንኛዉም ሰው በክልሉ ዉስጥ በማንኛዉም ህጋዊ በሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያ የመረጠዉን ሥራ የመሥራት መብት አለዉ፤

2. ማንኛውም ሰው በክልሉ ዉስጥ መተዳደሪያዉን፣ ሥራዉንና ሙያዉን የመምረጥ መብት አለዉ፤

3. ማንኛዉም በክልሉ ነዋሪ የሆነ ሰው በመንግስት በጀት በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አለው፤ መብቶቹም እንዲሟሉ የክልሉ መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን በየጊዜዉ እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል፤

4. የክልሉ መንግስት አካል ጉዳተኞችን፣የአእምሮ ጉዳተኞችን፣ የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንን፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ወይም አሳዳጊ የሌላቸው ህጻናትን እና ሌሎች ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማቋቋምና ለመርዳት አቅም በፈቀደ መጠን ድጋፍና ክብካቤ ያደርጋል፤

5. የክልሉ መንግስት በክልሉ ዉስጥ ለሚኖሩ ሥራ አጦችና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፤ እንዲሁም በሚካሄደዉ የሥራ ዘርፍ ዉስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል፤

6. መንግስት ለክልሉ ነዋሪዎች ሥራ የማግኘት ዕድላቸዉ እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግአስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

7. የክልሉ አርሶ አደሮች በየጊዜዉ እየተሻሻለ የሚሄድ ህይወት ለመኖርየሚያስችላቸውን ለምርት ካደረጉት አስተዋጽኦ ጋር ተመጣጣኝና ተገቢ የሆነ ዋጋ የማግኘት መብት አላቸዉ፤

8. በክልሉ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው በቂ ምግብ፣ልብስና መኖሪያ ቤትን ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ በሆነ የኑሮ ደረጃ ለመኖርና የኑሮ ሁኔታን ለማሻሻል መብት አለው፤

9. የክልሉ የብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህላቸውን፣ቅርሳቸውን እና ታሪካቸውን የመንከባከብ፣ የመጠበቅ እና የማስፋፋት መብት አላቸዉ፤

10. የክልሉ መንግስት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን በመንከባከብና በመጠበቅ ለሥነ-ጥበብ፤ ለምርምር፣ ለቱሪዝምና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤

11. የክልሉ መንግስት የብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ነባር የባህል አደረጃጀቶች እና ሀገር በቀል እውቀቶች የሚበለፅጉበትንና ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 43. የሠራተኞች መብት

1. የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሠራተኞች፣ ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች የስራ ሁኔታዎችን፣ ማህበራዊ እና የኢኮኖሚ ጥቅሞችን ለማስከበርና ለማሻሻል የመደራጀት መብት አላቸው፤ ይህ መብት የሠራተኛ ማኅበራትንና ሌሎች ማኅበራትን የማደራጀት፣ ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል፣

2. በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውንና አቤቱታቸውን የማሰማት መብት አላቸው፣

3. በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ።

4. ሠራተኞች፡-

ሀ) በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት፣

ለ) የዕረፍትና የመዝናኛ ጊዜ፣

ሐ) ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የዕረፍት ቀኖች፣

መ) ደመወዝ የሚከፈልባቸዉ የህዝብ በዓላት፣

ሠ) ጤናማና አደጋ የማያደርስ ስምቹ የሥራ አካባቢ የማግኘት፣

ረ) ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብት አላቸዉ።

5. በንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው መብት ለአካል ጉዳተኛ እና ለሴት ሠራተኞችም ተፈጻሚ ነው፤

6. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ልዩ ሕጎች በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት እዉቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የሠራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋሙበትና የህብረት ድርድርስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋል።

አንቀጽ 44.የመልማት መብት

1. የግልና የጋራ የመልማት መብት የተጠበቀ ነው፤

2. የመልማት ዋና ዓላማ የክልሉን ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ዕድገትና መሰረታዊ ፍላጎቶችን ማሟላት ነው፤

3. የክልሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የኑሮ ሁኔታቸዉን የማሻሻል እና ቀጣይነት ያለው እድገት የማግኘትመብት አላቸው፤

4. የክልሉ ነዋሪዎች ብሔራዊና ክልላዊ በሆኑ የልማት ሥራዎች ፣ዕቅድ፣ የልማት ፖሊሲ እና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይም የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ጥቅም በሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ የመሳተፍ እና ሀሳባቸውን የመግለጽ መብት አላቸው።

5. በልማት ወደ ኋላ የቀሩ አካባቢዎችና ማህበረሰቦች ተመጣጣኝ እድገት እንዲኖር ልዩ ትኩረት የማግኘት መብት አላቸው፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 45.የአካባቢ ደህንነት መብት

1.ማንኛውም ሰው ንጹህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አለው፤

2. የክልሉ መንግስት የአካባቢ ደህንነትን የመጠበቅ፣ የማስጠበቅና የተጎዱ አካባቢዎችን እንዲያገግሙ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤

3. በክልሉ ውስጥ የሚካሄድ ማንኛውም ፕሮጀክት ከመጀመሩ በፊት የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ተካሂዶ በአካባቢው እና በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

4. በንኡስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ቢኖርም የልማት ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች በነዋሪው ወይም በአካባቢው ላይ ሊሚያስከትሉት የጤና ችግር ወይም ጉዳት አካባቢውን የማከምና ወደ ቀድሞ ሁኔታው የመመለስን ሀላፊነት ጨምሮ ካሳ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

ምዕራፍ አራት

የክልሉ መንግስት አደረጃጀትና ስልጣን ክፍፍል

ክፍል አንድ

የክልሉ መንግስት አደረጃጀት

አንቀጽ 46. የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

የክልሉ መንግስት በክልሉ ዉስጥ በሚገኙት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መዋቅሮች የተመሰረተ ሲሆን፡-

1. በክልል፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር እና በቀበሌ አስተዳደር እርከኖች የተዋቀረ ነው፤

2. በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሌሎች አደረጃጀቶችን ሊያቋቁም እና ስልጣንና ተግባራቸውን ሊወሰን ይችላል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

3. የክልሉ መንግስት መስራች መዋቅሮች ዉስጥ ያሉት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልሉን በመመስረት ሂደት እኩል መብት እና ስልጣን አላቸዉ።

አንቀጽ 47. አዳዲስ አደረጃጀቶችን ስለመመስረት

1. በክልሉ የሚገኙ ማንኛዉም ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የራሳቸውን ክልል የመመስረት መብት አላቸው።

2. የማንኛዉም የክልሉ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የራሳቸውን ክልል የመመስረት መብት ሥራ ላይ የሚዉለዉ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት በተደነገገዉ አግባብ ይሆናል፤

3. የክልሉ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በማናቸዉም ጊዜ የራሳቸውን የዞን፣ የልዩ ወረዳ፣ የወረዳ፣ የከተማ አስተዳደር እና የቀበሌ አደረጃጀት መዋቅር የማቋቋም መብት አላቸው፤

4. በንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት የሚነሱ የዞን፣የልዩ ወረዳ፣የወረዳ፣የከተማ አስተዳደር እና የቀበሌ አደረጃጀት ጥያቄዎች የህዝቦችን ታሪክ፣ባህል፣ቋንቋ፣ማህበረሰባዊ መስተጋብር፣አሰፋፈር፣ ፍላጎት እና የጥቅም ቁርኝት መሰረት በማድረግ የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ህግ መሰረት ሲወሰን ነው፤

5. በንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንነትን መሰረት ያደረጉ የዞን፣የልዩ ወረዳ እና የወረዳ አደረጃጀት ጥያቄዎች ለክልሉ የብሔረሰቦች ምክር ቤት ቀርቦ የሚወሰን ሆኖ ይህ መብት ስራ ላይ የሚውለው የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች በአንድ ላይ ሲሟሉ ይሆናል፡-

   ሀ)የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አደረጃጀት ጥያቄ የመደራጀቱን ጥያቄ ያቀረበው የወረዳ ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት በ 2/3 ኛ ድምጽ ፀድቆና በምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ተፈርሞ ለክልሉ የብሔረሰቦች ምክር ቤት ሲቀርብ፣

   ለ) ጥያቄው በ 2/3 ኛ ድምጽ በክልሉ የብሔረሰቦች ምክር ቤት ሲረጋገጥ፣

   ሐ) የብሔረሰቦች ምክር ቤቱ ጥያቄዉ በቀረበ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፣

6. በንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከማንነት ጋር ያልተገናኙ የዞን፣ የልዩ ወረዳ እና ወረዳ አስተዳደር መዋቅር አደረጃጀት ጥያቄዎች ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው የሚወሰን ሆኖ ይህ መብት ስራ ላይ የሚውለው የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች በአንድ ላይ ሲሟሉ ይሆናል፡-

   ሀ) ከአንድ ዞን ወጥቶ የራሱን ዞን ለመመስረት የሚቀርብ ጥያቄ ጠያቂው አካል በሚገኝበት የወረዳ ምክር ቤት በ 2/3 ኛ ድምጽ ፀድቆና በምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ተፈርሞ ለዞን ተወካዮች ምክር ቤት ሲያቀርብ ፣

   ለ) ጥያቄው የቀረበለት ዞን ምክር ቤት ጥያቄውን ከተቀበለበት አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በ 2/3 ኛ ድምጽ ከደገፈ ለመጨረሻ ውሳኔ ለክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፤

   ሐ) በዞኑ ምክር ቤት ጥያቄው በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢዉ ወሰኔ ካልተሰጠ ጥያቄ አቅራቢው በቅሬታ ለክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይችላል፤

   መ) የክልሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄው ወይም ቅሬታው ከቀረበለት አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይወስናል፤

7. የወረዳ፣ የከተማ አስተዳደር እና የቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀት መዋቅር ጥያቄዎችን በተመለከተ የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ህግ መሰረት ተፈጻሚ ይደረጋል፤
8. በዚህ አንቀጽ በተደነገገው አግባብ የሚደራጀዉ አዲስ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለክልሉ መንግስት ይሆናል፤
9. ከመዋቅር አደረጃጀት ጋር በተገናኘ የንብረትና የእዳ ክፍፍል ስርዓት በተመለከተ በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጣ ህግ ተፈጻሚ ይሆናል፤
10. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቋቋሙ አባል መዋቅሮች እንዲሁም በመዋቅሮቹ ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በክልሉ እኩል እውቅና፣ ተመጣጣኝና ፍትሀዊ ስልጣን የማግኘት መብት አላቸው፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤

አንቀጽ 48. የአስተዳደር እርከኖች የወሰን አከላለል

1. በክልሉ ውስጥ የሚኖረውን የአስተዳደር እርከን ወሰን አከላለል የህዝቦችን ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ ፣ ማህበረሰባዊ መስተጋብር፣ አሰፋፈር፣ ፍላጎት እንዲሁም የጥቅም ቁርኝት መሰረት በማድረግ ወይም ሌሎች ተገቢ የሆኑ መስፈርቶችን የተከተለ ይሆናል፤
2. በክልሉ ውስጥ የአስተዳደር እርከን ወሰንን በሚመለከት አለመግባባት የተነሳ እንደሆነ በሚመለከታቸው መዋቅሮች ውስጥ ባሉ የአካባቢው ማህበረሰብ አካላት በስምምነት ይፈታል፤
3. በንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው አግባብ ጉዳዩ ካልተፈታ በየእርከኑ ባለው የአስተዳደር መዋቅር የሚፈታ ይሆናል፤
4. በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ያለመግባባቱ ካልተፈታ የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት ጉዳዩ በቀረበ አንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠውን መስፈርት በመከተል ውሳኔ ይሰጣል፤
5. በንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በብሔረሰቦች ምክር ቤት በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወይም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምላሽ ያላገኘ አካል ይግባኙን ለፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል።

ክፍል ሁለት

የክልሉ መንግስት አካላት እና የስልጣን ክፍፍል

አንቀጽ 49. የክልሉ መንግስት አካላት

1. **የክልሉ መንግስት** የህግ አዉጪ፣ የህግ አስፈጻሚ እና የህግ ተርጓሚ አካላት ይኖሩታል፤
2. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በክልሉ ከፍተኛ የስልጣን አካል እና የህግ አውጪ ሆኖ ተጠሪነቱ ለወከለው ሕዝብ ነው፤
3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በክልሉ ከፍተኛ ሕግ አስፈፃሚ አካል ሆኖ ተጠሪነቱም ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፤
4. የዳኝነት ስልጣን የክልል ፍርድ ቤቶች ነው።

አንቀጽ 50. የክልሉ መንግስት የስልጣን ክፍፍል መርህ

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች እኩል እዉቅና፣ተመጣጣኝና ፍትሃዊ ስልጣን የማግኘት መብት አላቸው፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤
2. በክልሉ ብቃትንና ብዝሀነትን ያማከለ ተመጣጣኝና ፍትሐዊ የስልጣን ክፍፍል ይኖራል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 51. የክልሉ መንግስት ስልጣንና ተግባር

1. የክልሉን ህገ መንግስት ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤ ይጠብቃል፤ ይከላከላል፤
2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስትን ይጠብቃል፣ይከላከላል፤
3. የዞን፣ የልዩ ወረዳ፣ የከተማ አስተዳደር፣ የወረዳዎች እና የቀበሌ የልማት እቅድን መሰረት በማድረግ የክልሉን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፤ ያጸድቃል፤ያስፈጽማል፤
4. የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሰረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፤
5. በክልሉ የተሰማሩ የአገር ዉስጥ ኢንቨስተሮችን የሚመለከት ህግ ያወጣል፤
6. በክልሉ ዉስጥ ኢንዱስትሪ ያቋቁማል፤ ያስተዳድራል፤ ህግ ያወጣል፣
7. በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ብዝሃ ህይወትን ይጠብቃል፣ ያስተዳድራል፤
8. መንግስታዊ የእርሻ ልማቶችን ያቋቁማል፣ያስተዳድራል፤
9. የጦር መሳሪያን በተመለከተ በፌዴራሉ ሕግ መሰረት ፈቃድ ይሰጣል፤
10. ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል፤
11. የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል፤
12. የክልሉን የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎችን በተመለከተ ህግ ያወጣል፣ያስፈጽማል፣ ብዝሀነትንም ያረጋግጣል ፤ ሆኖም ለአንድ የሥራ መደብ የሚያስፈልጉ የትምህርት፣ የሥልጠና፣ የልምድ እና ብቃት ማረጋገጫ መመዘኛዎችን በአጠቃላይ ከህገሪቱ መመዘኛዎች ጋር የተቀራረቡ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፤
13. የክልሉን የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ይመራል፣የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ያስጠብቃል፤
14. በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 30 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ መሠረት በክልሉ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር በሆኑ የወንጀል ቅጣት ጉዳዮች ይቅርታና ምህረት ያደርጋል፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤
15. በክልል መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፤ይሰበስባል፤
16. በክልሉ ውስጥ በህግ አግባብ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያዉጃል፤
17. ክልሉ የሚከተሉት የታክስ እና ግብር ስልጣኖች ይኖሩታል፤
    ሀ) በክልሉ የመንግስት እና የግል ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፤ይሰበስባል፣
    ለ) የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፤ይሰበስባል፣
    ሐ) የእርሻ ሥራ ግብር ይጥላል፤ይሰበስባል፣

መ) በክልሉ በግል ባለቤትነት ከተያዙ ቤቶችና ከሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ያስከፍላል፣ይሰበስባል፤

ሠ) በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት የተያዙ ቤቶችና ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል፣ ይሰበስባል፤

ረ) በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ከሚገኙ ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣የሥራ ግብር፣ የሽያጭ እና ኤክሳይዝ ታክስ ይጥላል፤ያስከፍላል፣ይሰበስባል፣

ሰ) በክልሉ በሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የንግድ ትርፍ ግብርና የሽያጭ ታክስ ይጥላል፤ ያስከፍላል፣ ይሰበስባል፣

ሸ) ክልሉ በሚያስተዳድረው በየብስና በውሀ ላይ በሚደረግ ትራንስፖርት በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፤ያስከፍላል፣ይሰበስባል፣

ቀ) የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 98 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በማዕድን ሥራዎች ላይ የማዕድን ገቢ ግብር፣ የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ ክፍያዎችን ይጥላል፤ይሰበስባል፤

በ) የፈጠራ ዉጤቶች ሽያጭ እና ኪራይ ሮያሊቲ ታክስ ይጥላል፤ይሰበስባል፤

ተ) በክልሉ ዉስጥ የሚገኝ የካርበን ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፤ይሰበስባል፤

ቸ) የቁም ከብት ሽያጭ ግብር ይጥላል፤ይሰበስባል፤

ኀ) በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ፓርኮች እና የቱሪዝም መስህቦች አገልግሎት ገቢ ግብር ይጥላል፤ ይሰበስባል፤

ነ) ሌሎች ታክሶችን ይጥላል፤ይሰበስባል።

18. ክልሉ ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር፡-

ሀ) በጋራ ከሚያቋቁማቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር፣የሥራ ግብር፣የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ በሕጉ መሠረት ይከፈላል፤

ለ) ከድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና ከባለ አክስዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ የግብርና የሽያጭ ታክስ በሕጉ መሠረት ይከፈላል፤

ሐ) ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማንኛውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በሕጉ መሠረት ይከፈላል፣

19. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ተለይተው ለፌዴራል መንግስት ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሉ መንግስት በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጪ ማናቸውም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ሥልጣን ይሆናል፤

20. የክልሉ መንግሥት በዚህ አንቀጽ ከተቀመጠው ስልጣንና ተግባር ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ለበታች የአስተዳደር እርከኖች፣ለክልሎችወይም ለፌዴራል መንግስት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

21. ልዩ ልዩ ህጎችን ያወጣል፤ ያስፈጽማል።

ምዕራፍ አምስት

የክልሉ መንግስት ምክር ቤቶች

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

አንቀጽ 52. የክልሉ መንግስት ምክር ቤቶች

የክልሉ መንግስት የክልል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል የብሔረሰቦች ምክር ቤት ይኖሩታል።

አንቀጽ 53.የምክር ቤቶች የወል ድንጋጌዎች

1. እያንዳንዱ ምክር ቤት፡-

ሀ) ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ የሆነ የራሱን አፈ-ጉባዔ እና ምክትል አፈ-ጉባዔ በምክር ቤቱ ዉስጥ አብላጫ ድምጽ ባገኘዉ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በምርጫ ይሰይማል፤ለሥራ የሚያስፈልጉ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያደራጃል፤

ለ) የሥራ ዘመኑ አምስት ዓመት ሆኖ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል።

2. እያንዳንዱ የምክር ቤት አባል፡-

ሀ) በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምፅ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፤ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፤

ለ) ከባድ ወንጀል ሲፈፅም እንጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም በወንጀልም አይከሰስም፤

ሐ) የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል፤ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ላይ የተደነገገው እንደ አግባብነቱ በየእርከኑ ለሚገኙ ምክር ቤቶች እና አባላት ተፈፃሚነት አለው፤

ሠ) አንድ ሰዉ በአንድ ጊዜ የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት አባል መሆን አይችልም።

ክፍል ሁለት

የክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባር

አንቀጽ 54. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት

1. ሁሉ አቀፍ፣ ነፃና ቀጥተኛ በሆነ፣ ድምጽ በምስጢር በሚሰጥበት ስርዓት በየአምስት ዓመቱ በህዝብ ይመረጣሉ፤
2. በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ስርዓት ይመረጣሉ፤
3. በንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ ውክልና የሚያስፈልጋቸዉ የማህበረሰብ ክፍሎች በምርጫ በክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ይወከላሉ፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤
4. የመላው የክልሉ ህዝብ ተወካዮች ናቸው። ተገዥነታቸውም፡-
   ሀ) ለኢፌዴሪ ሕገ መንግስት፣ለክልሉ ሕገ መንግስት እና ለህግ፤
   ለ) ለክልሉ ህዝብ፤ እና
   ሐ) ለራሳቸው ህሊና ብቻ ነዉ።

5.ማንኛዉም የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የወከለዉን ህዝብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን መከታተል፣ ለምክር ቤቱ ማሳወቅ እና መፍትሔ ለማስገኘት ጥረት ማድረግ አለበት፤

6. በዚህ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ያሉ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው በየእርከኑ ለሚገኙ የምክር ቤት አባላት ተፈፃሚነት አላቸው።

አንቀጽ 55. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት **ስልጣንና ተግባር**

1. የክልሉ ከፍተኛ የህግ አውጪ አካል ነው፤

2. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነው፤

3. የፌደራሉን ህገ መንግስት፣ ይህን ሕገ መንግስትና ሌሎች ህጎችን የሚፃረሩ ለክልሉ ተለይተዉ በተሰጡ እና በክልሉ ውስጥ ተፈፃሚ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ ህጎችን ያወጣል፤

4. በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 በተደነገገው አግባብ የአደረጃጀት ጉዳዮችን ይወስናል፤ዝርዝር ህጎችን ያወጣል፤

5. የፌደራል መንግስት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሉ ከሌሎች ክልል መንግስታት ጋር የሚደረገውን ስምምነት መርምሮ ያፀድቃል፤

6. በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ካለው ፖለቲካ ድርጅት የክልሉን ርዕሰ መስተዳድር ሹመት ያፀድቃሉ፤

7. በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላትን ሹመት ያፀድቃል፤

8. የክልሉን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ያፀድቃል፤

9. የክልሉን የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ህጎችን ያወጣል፤ ለክልሉ መንግስት ተለይቶ በተሰጠው የገቢ ምንጭ ላይ በክልሉ ውስጥ ግብርና ታክስ ይጥላል፤

10. የክልሉን መንግስት በጀት ያፀድቃል፤

11. የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ሥራዎች የሚያከናውኑ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ልዩ ልዩ ቢሮዎችን፣ ኮሚሽኖችንና ሌሎች መሥሪያ ቤቶችን እንደ አስፈላጊነታቸው በሕግ ያቋቁማል፤

12. የዳኞችን ሹመት በዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባኤ አቅራቢነት ያጸድቃል፤

13. በርዕሰመስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት ሹመት ያፀድቃል፤

14. የኦዲትና ሌሎች የቁጥጥር አካላትን ያቋቁማል፣ ዋና ኦዲተሩን እና ምክትል ዋና ኦዲተሩን ይሾማል፤

15. የዋና ኦዲተርና የቁጥጥር አካሉን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር በህግ ይወስናል፤

16. የክልሉን መንግስት ሰራተኞች አስተዳደርና የስራ ሁኔታዎችን በተመለከተ ህግ ያወጣል፤

17. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያፀድቃል፤

18. የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግስት ባለስልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፣ የአስፈፃሚውን አካል አሰራር ይመረምራል፤ የማስተካከያ ሀሳብና የሥራ አቅጣጫ ይሰጣል፤ አመኔታ ባጣ ጊዜም እርምጃ ይወስዳል፤

19. የራሱን ጽህፈት ቤት ያደራጃል፤

20. በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 30 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ መሠረት ምህረት ያደርጋል፤

21. የፖሊስ ሀይል ያደራጃል፤

22. ሌሎች የክልሉን መንግስት በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ህግ ያወጣል።

አንቀጽ 56. የፖለቲካ ስልጣን

1. በክልል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ያደራጃል፣ይመራል ወይም ያደራጃሉ፣ይመራሉ፤

2. በክልል የህዝብ ተወካይ ምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች ከክልሉ ህዝብ ተወካይ ምክር ቤት አባላት መካከል የምክር ቤቱን ዋና አፈ-ጉባዔንና ምክትል አፈ-ጉባዔን በማቅረብ ያሰይማል፣ያሰይማሉ፤

3. የዚህ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው በየእርከኑ ለሚገኙ ምክር ቤቶች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ 57. የክልል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት **ጽህፈት ቤት**

1. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የራሱ የሆነ አደረጃጀት ያለው ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ የሆነ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፤

2. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ሀላፊ በአፈ-ጉባኤው አቅራቢነት በአስተባባሪ ኮሚቴ ይሾማል፤

3. በምክር ቤቱ ስር ቋሚ ኮሚቴዎች ይደራጃሉ፤

4. የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባራት የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ህግ ይወሰናል፤

5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደ አግባብነቱ በየደረጃዉ ለተቋቋመ ምክር ቤት ተፈፃሚነት አለው።

አንቀጽ 58. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት **አፈ-ጉባዔ ስልጣንና ተግባር፣ የስልጣን ዘመን**

የክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፤ይመራል፤

2. ምክር ቤቱን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፤

3. የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ያደራጃል፤ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤

4. ምክር ቤቱ በአባሎች ላይ የወሰነውን የዲስፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል፤

5. የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት አደረጃጀት በህግ ያስወስናል፤

6. የምክር ቤቱን ጊዜያዊና ቋሚ ኮሚቴዎችን ያስተባብራል፤

7. በህግ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል፤

8. የአፈ- ጉባኤው የስልጣን ዘመን ለተከታታይ ሁለት የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው፤

9. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደ አግባብነቱ በየደረጃዉ ለተቋቋመ ምክር ቤት ተፈፃሚነት አለው።

አንቀጽ 59. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት **ምክትል አፈ-ጉባዔ ስልጣንና ተግባር**

የክልሉ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባዔ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአፈ-ጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

2. አፈ-ጉባዔው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

3. የአፈ- ጉባኤው የስልጣን ዘመን ለተከታታይ ሁለት የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

አንቀጽ 60. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት **የስብሰባ ጊዜ፣የሥራ ዘመን እና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት**

1. ምክር ቤቱ በዓመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤

2. ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ሁለት ሶስተኛ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፤

3. በዚህ ህገ መንግስት በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው ላይ ከተገኙት የምክር ቤት አባላት ውስጥ በአብላጫ ድምጽ ይሆናል፤

4. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አንድ የምርጫ ዘመን ይሆናል፤

5. ምክር ቤቱ የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፤

6. የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፤

7. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

8. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ-ጉባዔው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፤

9. የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፣ ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ከተጠየቀና ከምክር ቤቱ አባላት መካከልከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉ ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤

አንቀጽ 61. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት **የህግ አጸዳደቅ እና የአሰራር ስነ-ስርዓት**

1. ምክር ቤቱ መክሮበት በአብላጫ ድምጽ የተስማማበት ህግ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ለፊርማ ይቀርባል፤

2. ርዕሰ መስተዳድሩ በንዑስ አንቀጽ 1 የቀረበለትን ህግ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ካልፈረመ ህጉ በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ ታውጆ በሥራ ላይ ይዉላል፤

3. ምክር ቤቱ የህግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት ህግ ሊያወጣ ይችላል፤

4. የምክር ቤቱን የአሰራር ሥነ ሥርዓት እና የአባላት የስነ ምግባር ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣

5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንዳስፈላጊነቱ ለዞን፣ለልዩ ወረዳ፣ ለወረዳ፣ለከተማ አስተዳደር እና ለቀበሌ ምክር ቤቶች ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ 62. ስለ ክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መበተን

1. ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ ምክር ቤቱ የስልጣን ዘመን ከማብቃቱ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሔድ በክልሉ ምክር ቤት ፈቃድ ምክር ቤቱ እንዲበተን ለማድረግ ይችላል፣

2. በጣምራ የመንግሥት ሥልጣን የያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራነታቸው ፈርሶ በምክር ቤቱ የነበራቸውን አብላጫነት ያጡ እንደሆነ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተበትኖ በክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ ጣምራ መንግሥት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመመስረት እንዲቻል ርዕሰ መስተዳድሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ይጋብዛል፤

የፖለቲካ ድርጅቶቹ አዲስ መንግሥት ለመመስረት ወይም የነበረውን ጣምራነት ለመቀጠል ካልቻሉ የክልሉ ምክር ቤት ተበትኖ አዲስ ምርጫ ይደረጋል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 መሰረት የክልሉ ምክር ቤቱ የተበተነ እንደሆነ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ መደረግ አለበት፣

4. ምርጫው በተጠናቀቀ በሠላሳ ቀናት ውስጥ አዲሱ የክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፣

5. የክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተበተነ በኋላ ክልሉን የሚመራው ሥልጣን ይዞ የነበረው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራ የዕለት ተዕለት የመንግሥት ሥራ ከማከናወንና ምርጫ ከማካሔድ በስተቀር አዲስ አዋጆችን፣ ደንቦችንና ድንጋጌዎችን ማውጣት ወይም ነባር ሕጎችን መሻርና ማሻሻል አይችልም፣

6. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር እና በቀበሌምክር ቤቶች ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍልሦስት

የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት

አንቀጽ 63. የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት አባላት

1. የብሔረሰቦች ምክር ቤት በክልሉ የሚገኙት ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ቢያንስ በአምስት አባላት የሚወከሉበት ምክር ቤት ነዉ፤

2. ከእያንዳንዱ ብሔር፣ብሔረሰብ፣ ህዝብ ቢያንስ በአንድ ሚሊዮን ህዝብ አንድ ተጨማሪ አባላት ይወከላል፤

3. የብሔረሰቦች ምክር ቤት አባላት በዞን ወይም በልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች በአብላጫ ድምጽ ይመረጣሉ፤የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች በራሳቸው ወይም በቀጥታ በህዝብ እንዲመረጡ በማድረግ የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት አባል እንዲወከል ያደርጋል።

4. በንኡስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዞን ወይም በልዩ ወረዳ ያልተወከሉ በወረዳ ምክር ቤቶች በአብላጫ ድምጽ ጸድቆ ይወከላሉ።

አንቀጽ 64. የብሔረሰቦች ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የክልሉን ሕገ መንግስት ይተረጉማል፤

2. የክልሉን ሕገ መንግስት አጣሪ ጉባዔ ያደራጃል፤

3. የክልሉ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የዞን፣ የልዩ ወረዳ እና የወረዳ አስተዳደር መብት የሚነሱ ጥያቄዎች በዚህ ሕገ መንግስት መሰረት ይወሰናል፤

4. የክልሉን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተው አንድነት እንዲጠናከር እና እንዲጎለብት ያደርጋል፤

5. በክልሉ ውስጥ በሚገኙ አስተዳደር እርከኖች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሔ ያፈላልጋል፤ውሳኔ ይሰጣል፤

6. በክልሉ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች መካከል ሊነሱ የሚችሉ አለመግባባቶች እልባት እንዲያገኙ ያደርጋል፤ውሳኔ ይሰጣል፤

7. በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ልዩ ውክልና የሚያስፈልጋቸዉ ማህበረሰብ ክፍሎችን በህግ ይወስናል፤

8. የክልሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ በሚጎለብትበት ሁኔታ ላይ ይሰራል፤

9. የክልሉ ሕገ መንግስት ማሻሻያ ሀሳብ በማመንጨትና በማሻሻል ሂደት ዉስጥ ይሳተፋል፤

10. ከአጎራባች ክልል መንግስታት ጋር በሚነሱ አለመግባባቶች እና የወሰን መካለል ጥያቄዎች ከክልሎቹ ጋር በጋራ አጥንቶ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

11. **የራሱን በጀት** ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤

12. **የራሱ የሆነ አደረጃጀት ያለው፣ በዋና አፈ ጉባዔ አቅራቢነት የሚሾም፣ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ የሆነ ኃላፊ ያለው ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤**

13. የራሱን አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔ ይመርጣል፤

14. ልዩ ልዩ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን፣የስራ ክፍሎችን ያቋቁማል፤ ያስተዳድራል፤

15. የክልሉን የበጀት ቀመር ይወስናል፤ የበጀት ክፍፍል ፍትሀዊነትን፣የብሔሮች፣ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ተጠቃሚነትን ያረጋግጣል፣ይከታተላል፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 65. የውሳኔ እና ሥነ-ስርዓት ደንቦች

1. ከአባላቱ መካከል ሁለት ሶስተኛ የተገኙ እንደሆነ ምልዓተ ጉበዔ ይሆናል፤

2.ማንኛዉም የምክር ቤቱ ዉሳኔ ስብሰባ ላይ በተገኙ አባላት አብላጫ ድምጽ ይተላለፋል፤

3. የምክር ቤቱን የአሰራር ሥነ-ሥርዓት እና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 66. የብሔረሰቦች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ስልጣንና ተግባር፣ የስልጣን ዘመን

1. የምክር ቤቱን አስቸኳይ እና መደበኛ ስብሰባዎች ይጠራል፣ይመራል፤

2. ምክር ቤቱን ይወክላል፣ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን ይመራል፤

3. ምክር ቤቱ በአባላት ላይ የወሰደውን የዲስፒሊን እርምጃ ያስፈጽማል፤

4. የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ያደራጃል፤

5. የምክር ቤቱን ጊዜያዊና ቋሚ ኮሚቴዎችን ያስተባብራል፤

6. በምክር ቤቱና በህግ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

7. የአፈ- ጉባኤው የስልጣን ዘመን ለተከታታይ ሁለት የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

አንቀጽ 67. የብሔረሰቦች ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባዔ ስልጣንና ተግባር

1. አፈ-ጉባዔው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

2. በአፈ-ጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

3. የምክትል አፈ- ጉባኤው የስልጣን ዘመን ለተከታታይ ሁለት የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

ምዕራፍ ስድስት

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

አንቀጽ 68. የክልሉ መንግስት የአስፈጻሚነት ስልጣን

1. የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ስልጣን የተሰጠው ለርዕሰ መስተዳድሩ እና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነዉ፤

2. ርዕሰ መስተዳድሩ እና የመስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነታቸው ለክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነዉ፣

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በመንግስት ተግባራቸዉ በጋራ ለሚያሳልፉት ዉሳኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸዉ፣

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደ አግባብነቱ በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር፣ በወረዳ፣ በቀበሌ አስተዳደር አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ 69. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩና የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነዉ፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፣

2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ተጠሪነታቸዉም ለርዕሰ መስተዳድሩ ነዉ፤

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወስነዉ ዉሳኔ ለክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናል፤

4. የመስተዳድር ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ርዕሰ መስተዳድሩ ነዉ።

አንቀጽ 70. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

የፌደራል ህገ መንግስት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

1. በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በፌደራል መንግስት የወጡ ህጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በክልሉውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤መመሪያ ያወጣል፤

2. በህግ በሚወሰነው መሰረት የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት፣ሌሎች አስፈፃሚ አካላትና ሌሎች ተቋማት አደረጃጀት ይወስናል፤ሥራቸውን ይከታተላል፤ይመራል፤

3. የክልሉን መንግስት በጀት ያዘጋጃል፣ ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅ በስራ ላይያውላል፤

4. የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣የህግ ረቂቆችን ለክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፤የተወሰነውንም ያስፈፅማል፤

5. በክልሉ ውስጥ ህግና ስርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፤

6. የክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚሰጠው ስልጣን መሰረት ደንቦችን ያወጣል፤

7. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፣በዚህ ሕገ መንግስት በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፤

8. በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በህግ መሰረት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 71. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አሰያየምና የስልጣን ዘመን

1. ርዕሰ መስተዳደሩ በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘዉ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ብቃትን መሰረት በማድረግ ከክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት መካከል ይመረጣል፤
2. በዚህ ሕገ መንግስት በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር የርዕሰ መስተዳደሩ የሥራ ዘመን የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሥራ ዘመን ነዉ፤
3. በንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የርዕሰ መስተዳድሩ የስልጣን ዘመን ለተከታታይ ሁለት የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው፤
4. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በርዕሰ መስተዳድሩ ላይ እምነት ካጣበት በማንኛውም ጊዜ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ውሳኔ ከስልጣን ሊያነሳውና በምትኩ ሌላ ሊመርጥ ይችላል።

አንቀጽ 72. የርዕሰ መስተዳደሩ ስልጣንና ተግባራት

1. ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ መስተዳድር ሥራ መሪ፣ የመስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ እና የክልሉ ፕሬዝዳንት ነው፤
2. የንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ፡-

ሀ) የክልሉን መንግስት ይመራል፣ያስተባብራል፣ይወክላል፣

ለ) በክልሉ የፀደደቁ ህጎች ይፈርማል፣

ሐ) በክልሉ የወጡ ህጎችን፣ፖሊሲዎችን እና ውሳኔዎች ተፈፃሚነትን ይከታተላል፣

መ) የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሁም የክልሉን ዋና ኦዲተር እና ምክትል ዋና ኦዲተር ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል፣

ሠ) ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን ለክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል፤ የመስተዳድር ምክር ቤት አባላትን ከሁለቱ የክልሉ ምክር ቤቶች አባላት ወይም ለሥራው ብቃት ካላቸው ሌሎች ግለሰቦች መካከል ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዕጩነት በማቅረብ ያሾማል፣

ረ) በንዑስ አንቀፅ 2 (መ) እና (ሠ) ስር ከተዘረዘሩት ውጪ የሆኑ የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አስተዳደራዊ መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎችን እና ምክትል ኃላፊዎችን ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል፣

ሰ) የክልሉን ደህንነት ለመጠበቅ፣ህግንና ስርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፖሊስ ኃይሎችን በበላይነት ይመራል፣ይቆጣጠራል፣

ሸ) በክልሉ የሚገኙትን የበታች የመስተዳድር እርከኖችን ሥራ ይመራል፣ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

ቀ) የክልሉን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መስራች ጉባዔ ይጠራል፣ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፣

በ) በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 30 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ አግባብ ይቅርታ ያደርጋል፤

ተ) የክልሉን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የክልሉን የብሔረሰቦች ምክር ቤት ዓመታዊ የጋራ ስብሰባ ይከፍታል፤

ቸ) በህግ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 73. የምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ አሰያየም፣ሥልጣንና ተግባር፣የስልጣን ዘመን

የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጥ ሆኖ፦

1. ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለመስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፣
2. በርዕሰ መስተዳድሩ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
3. ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፤
4. የምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የስልጣን የሥራ ዘመን ለተከታታይ ሁለት የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

አንቀጽ 74.የርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት

1. ርዕሰ መስተዳድሩ የራሱ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፤
2. የርዕሰ መስተዳድሩ ጽህፈት ቤት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጽህፈት ቤት በመሆን ቁጥር ያገለግላል፤
3. ጽህፈት ቤቱ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚሾም አንድ የጽህፈት ቤት ኃላፊ ይመራል፤
4. የጽህፈት ቤት ኃላፊዉ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል፤
5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች አንደ የአስፈላጊነታቸው በተዋረድ ላሉ የመስተዳደር አካላት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 75. ስለ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ተቋማት መቋቋም

የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ሥራዎችን የሚያከናዉኑ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ልዩ ልዩ ቢሮዎች፣ ኮሚሽኖች፣ ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች፣ ኢንስቲትዩቶች፣ የአስተዳደር ወይም የልማት እና ሌሎች ተቋማት እንደ አስፈላጊነታቸዉ በህግ ይቋቋማሉ።

ምዕራፍ ሰባት

የዳኝነት ስልጣን

አንቀጽ 76. ስለ ዳኝነት አካል መቋቋም

1. በክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግስት ተቋቁሟል፤
2. የዳኝነትን ስልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጪ የሚያደርግና በሕግ የተደነገገውን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም፤
3. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ሕገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት እውቅና አግኝተዋል፤
4. የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሃይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላትን ሊያደራጅ ወይም እውቅና ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ 77. የዳኝነት ነፃነት

1. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግስት አካል፣ ባለስልጣን ወይም ሌላ አካል ተጽእኖ ነጻ ነው፤

2. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ፣ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፤

3. በንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባዔ በከባድ ወንጀል የተጠረጠሩ ወይም እጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲፈጽሙ የተያዙ ዳኞችን ያለመከሰስ መብታቸውን ያነሳል፤

4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሕግ የተወሰነው የጡረታ ዕድሜው ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነትሥራው አይነሳም፡-

ሀ) አግባብነት ያለው የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ በዳኞች የዲሲፕሊን ሕግ መሰረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ጉልህ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን፣ወይም

ለ) በህመም ምክንያት ዳኛው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስን ፣እና

ሐ) የጉባዔው የመጨረሻ ውሳኔ ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍና ሲጸድቅ።

5. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም፤

6. በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞችና በዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ የሚተዳደሩ ባለሙያዎች ምልመላ፤ የዲሲፕሊንና አስተዳደር ጉዳይ በህግ ይወሰናል፤

7. የዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ይዋቀራል፣ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤

8. **የክልሉ ፍርድ ቤቶች ከዳኞች ውጭ ያሉትን ሰራተኞች የመመልመል፣ የመቅጠርና የማስተዳደር ነፃነት አላቸው፤**

9. የክልሉ ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሠራተኞች ምልመላ ፣ ቅጥር ፣ምደባ ፣ እድገት ፣ ዝውውር ፣ ሥልጠና ፣ደመወዝ፣የጥቅማ ጥቅም ክፍያ እና የሠራተኞች የዲሲፕሊን ጉዳይ በክልሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጣ ህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 78. የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ሥልጣን

1. የዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የክልሉ የዳኝነትሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፤

2. የክልሉ ዳኝነት አካል በጠቅላይ ፍርድ ቤት፣በከፍተኛ ፍርድ ቤት፣በወረዳ ወይም በከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ይደራጃል፤

3. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣የከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የወረዳ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት፣ተግባርና ስልጣን በተመለከተ በህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 79. የክልሉ የፍርድ ቤቶች ፕሬዘዳንቶች እና ዳኞች አሿሿም

1.ዳኞች እና የፍርድ ቤቶች ፕሬዘዳንቶች ሹመት ስነ ምግባርን፣የሙያ ብቃትንና የብዝሀነት ስብጥርን መሰረት በማድረግ ይሆናል፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት ለዳኝነት ብቁ ከሆኑት መካከል በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፤

3. የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት እና የወረዳ ወይም የከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንት በየደረጃው ከዳኞች መካከል በዞን ወይም በልዩ ወረዳ አስተዳዳሪ አቅራቢነት በዞን ወይም በልዩ ወረዳ ምክር ቤት ይሾማሉ፤

4. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት ፣የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንቶች፣የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንቶች ኃላፊነቶች የአገልግሎት ዘመን አምስት አመት ሆኖ ከሁለት ጊዜ በላይ መሾም አይችሉም፤

5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣የከፍተኛ ፍርድ ቤት፣የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባዔ አቅራቢነት በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰ□ል።

አንቀጽ 80. ስለ ክልሉ ዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምጽ የሚወከሉበት፣ ነፃና ገለልተኛ የሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች የሚሳተፉበት፣ የራሱ አደረጃጀት ያለው፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሰብሳቢነት የሚመራ የክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባዔ በዚህ ህገ መንግስት ተቋቁሟል፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችና በጉባዔ የሚተዳደሩ ባለሙያዎችን የዲሲፕሊን፣ ዝውውርና ደረጃ ዕድገት ጉዳይ አይቶ የሚወስን የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት አስተዳደር ንዑስ ጉባዔ ይደራጃል፤
3. የከፍተኛው ፍርድ ቤትና በስሩ ያሉትን ፍርድ ቤቶች ዳኞች እና በጉባኤ የሚተዳደሩ ባለሙያዎችን ምልመላ፣ ዲሲፕሊንና አስተዳዳራዊ ጉዳዮችን አይቶ የሚወስን በከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የሚመራ የዳኝነት አስተዳደር ንዑስ ጉባዔ በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ይደራጃል፤
4. በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ የሚነሳን ቅሬታ በክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባኤ በይግባኝ ይታያል፤
5. የክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ዋና ጉባዔ፣የጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኝነት አስተዳደር ንኡስ ጉባኤ አደረጃጀት፣የአባላት ስብጥር፣ስልጣንና ተግባር በዝርዝር ህግ ይወሰናል።

ምዕራፍ ስምንት

ህገ መንግስት መተርጎም፣ ህገመንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ መቋቋም እና ሥልጣንና ተግባር

አንቀጽ 81. ህገ መንግስትን ስለ መተርጎም

1. በክልሉ ውስጥ የሕገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ወይም የትርጉም ጥያቄ ሲነሳ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሚያቀርብለት የውሳኔ ሃሳብ መሰረት የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤
2. የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት በንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት የሚያሳልፈው ውሳኔ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ መደገፍ አለበት፤
3. የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት በህገ መንግስት ትርጉም ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ አጠቃላይ ውጤት ይኖረዋል፣ወደ ፊት በክልሉ በሚነሱ ተመሳሳይ ህገ መንግስታዊ ጉዳዮች ላይ አስገዳጅነት አለው፤
4. በክልሉ የብሔረሰቦች ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ወደ ፌደሬሽን ምክር ቤት ይግባኝ የማለት መብት አለው፤
5. በዚህ አንቀጽ የተደነገገውን አስመልክቶ የብሔረሰቦች ምክር ቤት የራሱ የአሰራር ሥነ-ስርዓት ይኖረዋል፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 82. የክልሉ ህገ መንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ መቋቋም

1. የክልሉ ሕገ መንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በዚህ ሕገ መንግስት ተቋቁሟል።

2. የክልሉ ሕገ መንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አስራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሆኖ፡-

ሀ) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፣ ሰብሳቢ፣

ለ) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ሰብሳቢ፣

ሐ) በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወከሉ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ-ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የህግ ባለሙያዎች፣

መ) የብሔረሰቦች ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል የሚወክላቸው ሦስት አባላት ናቸው።

አንቀጽ 83.የሕገ መንግስት ጉዳዮች የአጣሪ ጉባዔ ስልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ሕገ መንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ከክልሉ የሚመነጩ ህገ መንግስታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ስልጣን አለው፤

2. በጉባዔው በሚደረገው ማጣራት መሠረት የክልሉን ሕገ መንግስት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳዩ ላይ የራሱን የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለብሔረሰቦች ምክር ቤት ያቀርባል፤

3. በፍርድ ቤቶች የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ ጉባዔው፡-

ሀ) የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ሕገ መንግስታዊ ትርጉም አሰናድቶ ለብሔረሰቦች ምክር ቤት ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል፤

ለ) የክልሉን ሕገ መንግስት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይመልሳል፤

ሐ)በአጣሪ ጉባዔ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ባለጉዳይ ይህንኑ ቅሬታውን በጽሑፍ አዘጋጅቶ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለብሔረሰቦች ምክር ቤት በይግባኝ ማቅረብ ይችላል፤

መ) በፍርድ ቤት ክርክር ወቅት የሕገ መንግስት ክርክር ጉዳይ ወይም ትርጉም ጥያቄ ጉዳይ ከተነሳ በብሔረሰቦች ምክር ቤት ዉሳኔ እስኪሰጥ የብሔረሰቦች ምክር ቤት የፍርድ ቤት ክርክር ሂደት እነደ አስፈላጊነቱ ታግዶ ሊቆይ ይችላል ወይም ጊዜያዊ ትዕዛዞችን ሊያስተላልፍ ይችላል።

4. ማንኛዉም ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ተቋም ሕገ መንግስታዊ ክርክር ጉዳይ ወይም ትርጉም ጥያቄ የሚመለከቱአቤቱታዎችን ለአጣሪ ጉባዔዉ ሊያቀርብ ይችላል፤

5. በንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደ አስፈላጊነቱ ለንዑስ አንቀጽ 4 ተፈጻሚ ይሆናል፤

6. የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት የሚሰጣቸዉን የሕገ መንግስት ትርጉም ዉሳኔዎችን ያሳትማል፤ ያሰራጫል።

ምዕራፍ ዘጠኝ

የዞን፣የልዩ ወረዳ፣የወረዳ፣የከተማ አስተዳደር እና የቀበሌ አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባር

ክፍል አንድ

የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር

አንቀጽ 84. የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አደረጃጀት

1. **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ መዋቅር** ከክልል ቀጥሎ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው፤

2. እያንዳንዱ **ዞን ወይም ልዩ ወረዳ** የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ምክር ቤት፣

ለ) የአስተዳደር ምክር ቤት፣

ሐ) የዳኝነት አካል።

3. **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** ሥልጣን ክፍፍል ብዝሃነትንና ፍትሀዊነትን ማስተናገድ በሚቻል መልኩ መሆን አለበት፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 85. የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** ምክር ቤት ለክልል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመረጡትን አባላት ጨምሮ ከየወረዳው ለዞን ወይም ለልዩ ወረዳ ምክር ቤት የሚመረጡ አባላት ያሉበት ሆኖ ይቋቋማል፤

2. **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** ምክር ቤት በደረጃው የበላይ የፖለቲካ ስልጣን አካል ነው፤

3. የንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** ምክርቤት ተጠሪነቱ ለመረጠው ህዝብ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) **የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን** የስራ ቋንቋ ይወስናል፣

ለ) ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በቋንቋቸው ለመናገር፣ ለመጻፍ፣ ቋንቋቸውን ለማሳደግ እንዲሁም ታሪካቸውን ለመንከባከብ ያላቸውን መብት ያስጠብቃል፣ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

ሐ) በዚህ ሕገ መንግስት ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖበፌዴራልና በክልል በወጡ ሕጎች ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ እነዚህን ህጎች በማይፃረር መልኩ ሕጎችን ያወጣል፣

መ) የክልል **የህዝብ ተወካዮች** ምክር ቤት ያጸደቀውን ዕቅድ እና በጀት መሰረት በማድረግ **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** እቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣

ሠ) **ከዞን ወይም ከልዩ ወረዳ የህዝብ ተወካዮች** ምክር ቤት አባላት መካከል አፈ-ጉባዔውን፣ ምክትል አፈ-ጉባዔውን እና ዋና አስተዳዳሪውን መርጦ ይሰይማል፤

ረ) በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ያስጸድቃል፣

ሰ) የከፍተኛ እና የወረዳ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶችንና ምክትል ፕሬዝዳንቶችን በዋናአስተዳዳሪዉ አቅራቢነት ይሾማል፤

ሸ) **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** ዋና አስተዳዳሪ፣ ሌሎች ባለስልጣናትንና የሥራ ኃላፊዎችን ለጥያቄ ይጠራል፤ አሰራራቸውን ይመረምራል፣ የማስተካከያ ሀሳብና የሥራ መመሪያ ይሰጣል፣ ከኃላፊነትምሊያነሳ ይችላል።

አንቀጽ 86. የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት አመራርና አፈ ጉባዔ

1. **የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት በምክር ቤቱ** አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ተመርጦ በሚሰየም አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ ጉባዔ ይመራል፤
2. በዚህ ሕገ መንግስት ስለ ክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር የተደነገገው **ለዞን ወይም ለልዩ ወረዳ ምክር ቤት** አፈ-ጉባዔ እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፤
3. ምክር ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያደራጃል፤
4. የአፈ- ጉባኤ የስልጣን ዘመን ለተከታታይ ሁለት የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

አንቀጽ 87. የዞን ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜና የስራ ዘመን እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ምክርቤቱ **በየአራት ወሩ** መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤
2. ከምክር ቤቱ አባላት ሁለት ሶስተኛው ከተገኘ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤
3. በዚህ ህገ መንግስት በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው ላይ ከተገኙት የምክርቤት አባላት ውስጥ በአብላጫ ድምጽ ይሆናል፤
4. የምክርቤቱ የሥራ ዘመን አንድ የምርጫ ዘመን ይሆናል፤
5. ምክር ቤቱ የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል፤
6. የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፤
7. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤
8. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባዔው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፤
9. የምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፣ ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ከተጠየቀና ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉ ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤

አንቀጽ 88. የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት

1. **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** ከፍተኛ የህግ አስፈጻሚ አካል የአስተዳደር ምክር ቤት ነው፤
2. **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** የአስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለዞኑ ወይም ለልዩ ወረዳው ምክር ቤት እና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፤
3. **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** አስተዳደር ምክር ቤት ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪና በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ውስጥ የሚገኙ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ሆኖ ተቋቁሟል፤
4. **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በጋራ ለወሰኑት ውሳኔና በፈጸሙት ተግባር የጋራ ሃላፊነትና ተጠያቂነት አለባቸው፤
5. **በዚህ ሕገ መንግስት ለርዕሰ መስተዳደሩን ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት ድንጋጌዎች የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን ዋና አስተዳዳር ጽሕፈት ቤት በሚመለከት እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።።**

አንቀጽ 89. የዞን ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

የአስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በፌዴራል፣ በክልሉ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና **በዞን ወይም በልዩ ወረዳ** ምክር ቤት የወጡ ህጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

2. የሌሎች አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ይወስናል፤ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፣

3. **የበጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ለዞኑ ወይም ለልዩ ወረዳው** ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲጽድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

4. **በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳ** ውስጥ ህግና ስርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፤

5. **በዞን ወይም በልዩ ወረዳ** ምክር ቤት፣ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እና በህግ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 90. የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና የስልጣን ዘመን

1. ዋና አስተዳዳሪው **በዞን ወይም በልዩ ወረዳ** ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ከዞኑ ወይም ከልዩ ወረዳው ምክር ቤት አባላት መካከል በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ምክር ቤት ይሰየማል፤

2. የዋና አስተዳዳሪው የስልጣን ዘመን ለተከታታይ ሁለት የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

አንቀጽ 91. የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

1. ዋና አስተዳዳሪው **የዞን ወይም የልዩ ወረዳ** አስተዳደር የሥራ መሪ፣ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሳቢና ዋና አስተዳዳሪ ነው፤

2. ዋና አስተዳዳሪው **ለዞን ወይም ለልዩ ወረዳ** ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ተጠሪ ሆኖ፦

ሀ) የዞኑን አስተዳደር ምክር ቤት ይመራል፤ይወክላል፤

ለ) የፌደራሉንና የክልሉን ሕገ መንግስት፣ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች **በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው** ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) **የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳ** አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያሾማል፣

መ) የዞኑን **ወይም የልዩ ወረዳው** ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ ህግና ስርዓት ለማስከበር የቀሙትን የፖሊስ ሀይል በበላይነት ይመራል፤ይቆጣጠራል፤

ሠ) አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶችን እና የበታች አስፈፃሚ እርከኖችን ይመራል፣ይቆጣጠራል፣

ረ) በደረጃው ላለው ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳደር በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፣

ሰ) የዞኑን **ወይም የልዩ ወረዳውን** ምክር ቤት መስራች ጉባኤ ይጠራል፤

ሸ) በደረጃው ባለው ምክር ቤትና በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የተሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 92. የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር፣ የስልጣን ዘመን

ምክትል ዋና አስተዳዳሪዉ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪና ለአስተዳደር ምክር ቤት ሆኖ፦

1. በዋና አስተዳዳሪውና በአስተዳደር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

2. ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

3. የምክትል ዋና አስተዳዳሪው የስልጣን ዘመን ለተከታታይ ሁለት የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

ክፍል ሁለት

የወረዳ አደረጃጀትና ስልጣን

አንቀጽ 93.የወረዳ አደረጃጀት

1. ወረዳ ከዞን ቀጥሎ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው።

2. እያንዳንዱ ወረዳ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

   ሀ. ምክር ቤት፣

   ለ. የአስተዳደር ምክር ቤት፣

   ሐ. የዳኝነት አካል።

6. የወረዳ ሥልጣን ክፍፍል ብዝሃነትንና ፍትሀዊነትን ማስተናገድ በሚቻል መልኩ መሆን አለበት፣ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀጽ 94. የወረዳ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

1. **የወረዳ አስተዳደር በተደራጀበት ክልል ውስጥ የኢኮኖሚያዊ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ዕቅድችን ለማዘጋጀትና ለመወሰንም ሆነ የክልሉ መንግስት አካላት በየጊዜው የሚያወጧቸውን ፖሊሲዎች፣ህጎች፣ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ማናቸውም ሥልጣን ይኖረዋል፤**

2. **እያንዳንዱ ወረዳ አስተዳደር አካባቢውን የማልማትና በውስጣዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠት መብትና ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መስተዳደሩ የተደራጀበት ዞን የበታች አካል ነው፡፡**

አንቀጽ 95. የወረዳ ምክር ቤት አባላት አመራረጥና ተጠሪነት

1) የወረዳ ምክር ቤት አባላት ወረዳው የተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በህዝብ የሚመረጡ ይሆናል፤

2) ምክር ቤቱ በተቋቋመበት ወረዳ ውስጥ ከፍተኛው መንግስታዊ የስልጣን አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለመረጠው ህዝብ ነው፤

አንቀጽ 96. የወረዳ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1. የወረዳውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች፣የልማትና አስተዳደራዊ የሥራ ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞችና በጀት ረቂቅ መርምሮ ያጸድቃል፣
2. በወረዳ ውስጥ መሰረታዊ የግብርና ልማት ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሄዳቸውንና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መከናወኑን ይከታተላል፣
3. ነዋሪው ህዝብ ለልማት ስራ በስፋት የሚነሳሳበትንና የሚንቀሳቀስበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፣
4. ከምክር ቤት አባላት መካከል አፈ-ጉባኤውን፣ ምክትል አፈ-ጉባኤውን እና ዋና አስተዳዳሪውን በምርጫ ይሰይማል፣

5. በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርብለትን የወረዳ አስተዳደርምክር ቤት አባላት ሹመት ያጸድቃል፣
6. የራሱን ውስጣዊ አስተዳደራዊ አሰራር ስነ-ስርዓት መመሪያ ያወጣል፣
7. የመሬት መጠቀሚያ ታክስን፣ የእርሻ ስራ ገቢ ግብርን፣የግብርና ውጤቶች ሽያጪ ግብርና ሌሎች የአገልግሎት ታክሶችና ክፍያዎችመሰብሰባቸውን ያረጋግጣል፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤
8. ክልሉ ከሚመድበውና ከሚያስተዳድረው ውጪ ያለውን የወረዳውን ገቢ ምንጭይጠቁማል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፣
9. የወረዳውን ዋና አስተዳዳሪ፣ ሌሎች ባለስልጣናትንና የሥራ መሪዎችን ለጥያቄ ይጠራል፣አሰራራቸውንም ይመረምራል፣ የሥራ አቅጣጫ ይሰጣል፤ ከኃላፊነትም ሊያነሳይችላል።

አንቀጽ 97.የወረዳ ምክር ቤት አመራርና አፈ ጉባዔ

1. የወረዳ ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ከምክር ቤቱ አባላት ተመርጦ በሚሰየም አፈ ጉባዔ እና ምክትል አፈ ጉባዔ ይመራል፤
2. በዚህ ሕገ መንግስት ስለ ክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት ለወረዳ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፤
3. የአፈ- ጉባኤው የስልጣን ዘመን ለአንድ የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

አንቀጽ 98. የወረዳ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባዔ

1. ምክትል አፈ-ጉባዔው በአፈ ጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
2. አፈ-ጉባዔው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
3. የምክትል አፈ-ጉባኤው የስልጣን ዘመን በአንድ የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

አንቀጽ 99. የወረዳ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜ፣ የስራ ዘመን እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ምክር ቤቱ **በየሶስት ወሩ** መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤
2. ከምክር ቤቱ አባላት ሁለት ሶስተኛው ከተገኘ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤
3. በዚህ ህገ መንግስት በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው ላይ ከተገኙት የምክርቤት አባላት ውስጥ በአብላጫ ድምጽ ይሆናል፤
4. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አንድ የምርጫ ዘመን ይሆናል፤
5. ምክር ቤቱ የሥራዘመኑከማብቃቱከአንድወርበፊትአዲስምርጫተካሂዶይጠናቀቃል፤
6. የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፤
7. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤
8. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባዔው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፤
9. የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፤ ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ከተጠየቀና ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉ ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤

አንቀጽ 100. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት

1. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለወረዳው ምክር ቤት ነው፤

2. የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ እና የወረዳው አስፈጻሚ መስሪያ ቤት ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው።

3. **በዚህ ህገ መንግስት የርዕሰ መስተዳደሩን ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት ድንጋጌዎች የወረዳውን ዋና አስተዳዳር ጽሕፈት ቤት በሚመለከት እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።**

አንቀጽ 101. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የፌዴራሉና የክልሉ መንግስት ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ እቅዶችና ፕሮግራሞች በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

ለ) የአስፈጻሚ አካላት ጽሕፈት ቤቶችን በበላይነት ያስተባብራል፤ ሥራቸውን ይከታተላል፤ ይመራል፤

ሐ) የወረዳውን በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፤ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያድረጋል፤

መ) የወረዳውን ሰላምና ጸጥታ ይጠብቃል፤ የወረዳውን የፖሊስ አካላት ይመራል፤

ሠ) የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያስጸድቃል፤

ረ) የተፈጥሮ ሀብትን ይጠብቃል፣ ያለማል፣ ይንከባከባል፣ ህዝቡን ለልማት ሥራ በስፋት ያነሳሳል፤

ሰ) በወረዳው ምክር ቤትና በዞኑ አስተዳደር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በመንግስታዊ ስልጣናቸው ለሚፈጽሙት ተግባርና በጋራ ለሚያሳልፉት ውሳኔ ኃላፊና ተጠያቂዎች ናቸው።

አንቀጽ 102. የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና የስልጣን ዘመን

1. ዋና አስተዳደሪው በወረዳው ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በወረዳ ምክር ቤት ይሰየማል፤

2. የዋና አስተዳዳሪው የስልጣን ዘመንበአንድ የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

አንቀጽ 103. የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

1. ዋና አስተዳዳሪ የወረዳው አስተዳደር ስራ መሪ፣ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሳቢና የወረዳው አስተዳደሪ ነው።

2. ዋና አስተዳዳሪው ለወረዳ ምክር ቤትና ለዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪ ሆኖ፦

ሀ) የወረዳውን አስተዳደር ይወክላል፤

ለ) የአስተዳደር ምክር ቤትን ይመራል፤

ሐ) የፌዴራሉንና የክልሉን ፖሊሲዎችና ህጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

መ) የአስተዳደር ምክር ቤት አባላትንና ሌሎች ልዩ ልዩ ተቋማትንና በስሩ የሚገኙትን ቀበሌዎች በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ሠ) የወረዳው ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና ዕቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል፣ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

ረ) የወረዳውን ነዋሪ ህዝብ ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ህግና ስርዓትን እንዲያስከብር የተቋቋመውን የፖሊስ ኃይል በበላይነት ይመራል ፣ይቆጣጠራል፣

ሰ) ለወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት፤ ለወረዳው ምክር ቤትና ለዞን አስተዳደር በየጊዜ ሪፖርት ያቀርባል፣

ሸ) የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል፤

ቀ) የወረዳውን ምክር ቤት መሰራት ጉባኤ ይጠራል፤

በ) በወረዳ ምክር ቤትና ዞን አስተዳደር ምክር ቤት የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 104. ስለ ወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር፣ የስልጣን ዘመን

የወረዳው ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪና ለወረዳ አስፈጻሚ ምክር ቤት ሆኖ፦

1. ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፤

2. የወረዳው አስፈጻሚ ምክር ቤትና ዋና አስተዳዳሪው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

3. የምክትል አስተዳዳሪው የስልጣን ዘመን በአንድ የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

ክፍል ሦስት

የከተማ አስተዳደር አደረጃጀትና ስልጣን

አንቀጽ 105. የከተማ አስተዳደር አደረጃጀት

1. በዞን ወይም በልዩ ወረዳ ደረጃ ሊዋቀር የሚችል **የከተማ አስተዳደር** መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማ አስተዳደር በወረዳ ደረጃ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው፤ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፤

2. እያንዳንዱ **ከተማ አስተዳደር** የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦

ሀ. ምክር ቤት፣

ለ. የአስተዳደር ምክር ቤት፣

ሐ. የዳኝነት አካል።

3.**የከተማ አስተዳደር** ሥልጣን ክፍፍል ብዝሃነትን ማስተናገድ በሚቻል መልኩ መሆን አለበት።

አንቀጽ 106. የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

1. **የከተማ አስተዳደር በተደራጀበት ክልል ውስጥ የኢኮኖሚያዊ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ዕቅድችን ለማዘጋጀትና ለመወሰንም ሆነ የክልሉ መንግስት አካላት በየጊዜው የሚያወጧቸውን ፖሊሲዎች፣ህጎች፣ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ማናቸውም ሥልጣን ይኖረዋል፤**

2. **እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር አካባቢውን የማልማትና በውስጣዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠት መብትና ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መስተደደሩ የተደራጀበት ዘንን የበታች አካል ነው።።**

አንቀጽ 107. የከተማ ምክር ቤት አባላት አመራረጥና ተጠሪነት

1. **የከተማ** ምክር ቤት አባላት ከተማው በተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በህዝብ የሚመረጡ ይሆናል፤
2. ምክር ቤቱ በተቋቋመበት **የከተማ አስተዳደር** ውስጥ ከፍተኛው መንግስታዊ የስልጣን አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለመረጠው ህዝብ ነው።።

አንቀጽ 108. የከተማ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. **የከተማ** ምክር ቤት አባላት ከተማው የተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በህዝብ የሚመረጡ ይሆናል፤

2. ምክር ቤቱ በተቋቋመበት **የከተማ አስተዳደር** ውስጥ ከፍተኛው መንግስታዊ የስልጣን አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለመረጠው ህዝብ ነው፤

3. የንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

ሀ) **የከተማ አስተዳደርን** ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ አገልግሎቶችና የልማትና አስተዳደራዊ የሥራ ዕቅዶች ፕሮግራሞችና በጀት ረቂቅ መርምሮ ያጸድቃል፤

ለ) በ**ከተማ አስተዳደር** ውስጥ መሰረታዊ የግብርና ልማት ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሄዳቸውንና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መከናወኑን ይከታተላል፤

ሐ) ነዋሪው ህዝብ ለልማት ስራ በስፋት የሚነሳሳበትንና የሚንቀሳቀስበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፤

መ) ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አፈ-ጉባኤውን፣ምክትል አፈ-ጉባኤውን እና ዋና አስተዳዳሪውን በምርጫ ይሰይማል፤

ሠ) በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርብለትን የከተማ አስተዳዳር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያጸድቃል፣

ረ) የራሱን ውስጣዊ አስተዳደራዊ አሰራር ስነ-ስርዓት መመሪያ ያወጣል፣

ሰ) የመሬት መጠቀሚያ ታክስ እና ሌሎች የአገልግሎት ታክሶችና ክፍያዎች መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፣

ሸ) ክልሉ ከሚመድበውና ከሚያስተዳድረው ውጪ ያለውን **የከተማ አስተዳደርን** ገቢ ምንጭ ይጠቁማል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፣

ቀ) **የከተማ አስተዳደርን** ዋና አስተዳዳሪ፣ ሌሎች ባለስልጣናትንና የሥራ መሪዎችን ለጥያቄ ይጠራል፣ አሰራራቸውንም ይመረምራል፣ የሥራ አቅጣጫ ይሰጣል፣ ከኃላፊነትም ሊያነሳ ይችላል።።

አንቀጽ 109. የከተማ ምክር ቤት አመራርና አፈ ጉባዔ

1. **የከተማ ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ተመርጦ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በሚሰየም አፈ ጉባዔ እና ምክትል አፈ ጉባዔ ይመራል፤**
2. በዚህ ህገ መንግስት ስለ ክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት ለ**ከተማ አስተዳደር** ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፤
3. የአፈ- ጉባኤው የስልጣን ዘመን በአንድ የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

አንቀጽ 110. የከተማ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባዔ

1. ምክትል አፈ-ጉባዔው በአፈ ጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
2. አፈ-ጉባዔው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
3. የምክትል አፈ-ጉባኤው የስልጣን ዘመን በአንድ የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

አንቀጽ 111. የከተማ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜ፣ የስራ ዘመን እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ምክር ቤቱ **በየሶስት ወሩ** መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤
2. ከምክር ቤቱ አባላት ሁለት ሶስተኛው ከተገኘ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤
3. በዚህ ህገ መንግስት በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው ላይ ከተገኙት የምክር ቤት አባላት ውስጥ በአብላጫ ድምጽ ይሆናል፤
4. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አንድ የምርጫ ዘመን ይሆናል፤
5. ምክር ቤቱ የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፤
6. የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ አዲሱም ክርቤት ሥራውን ይጀምራል፤
7. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤
8. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባዔው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፤
9. የከተማ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፣ ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ከተጠየቀና ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉ ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

አንቀጽ 112. የከተማ አስተዳደር ምክር ቤት

1. **የከተማ አስተዳደር** ምክር ቤት በተቋቋመበት **የከተማ አስተዳደር** ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም **ለከተማ** ዋና አስተዳዳሪና **ለከተማ አስተዳደር** ምክር ቤት ነው፤

2. **የከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የከተማ ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ እና የከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ መስሪያ ቤት ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው።**

3. **በዚህ ሕገ መንግስት የርዕሰ መስተዳደሩን ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት ድንጋጌዎች የከተማ አስተዳዳር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት በሚመለከት እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።**

አንቀጽ 113. የከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. **የከተማ አስተዳደር** ምክር ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የፌዴራሉና የክልሉ መንግስት ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ እቅዶችና ፕሮግራሞች በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

ለ) የአስፈጻሚ አካላት ጽሕፈት ቤቶችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፤

ሐ) **የከተማ አስተዳደርን** በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

መ) **የከተማ አስተዳደርን** ሰላምና ጸጥታ ይጠብቃል፣**የከተማ አስተዳደርን** የፖሊስ አካላት ይመራል፤

ሠ) የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ **ለከተማ አስተዳደር** ምክር ቤት በማቅረብ ያጸድቃል፤

ረ) የተፈጥሮ ሀብትን ይጠብቃል፤ ያለማል፤ ይንከባከባል፤ ህዝቡን ለልማት ሥራ በሰፋት ያነሳሳል፤

ሰ) በ**ከተማ አስተዳደር** ምክር ቤትና በዞን ወይም በልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትያከናውናል።

2. **የከተማ አስተዳደር** ምክር ቤት አባላት በመንግስታዊ ስልጣናቸው ለሚፈጽሙት ተግባርና በጋራ ለሚያሳልፉት ውሳኔ ኃላፊና ተጠያቂዎች ናቸው።

አንቀጽ 114. የከተማ አስተዳደር ከንቲባ አሰያየም

1. ከንቲባው በከተማ ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በከተማ ምክር ቤት ይሰየማል፤

2. የከንቲባውየስልጣን ዘመን በአንድየምርጫዘመንየተገደበ ነው።

አንቀጽ 115. የከተማ አስተዳደር ከንቲባ ስልጣንና ተግባር

1. ከንቲባዉ የከተማ አስተዳደር ስራ መሪ፣ የአስተዳደሩ ምክር ቤት ሰብሳቢና **የከተማ አስተዳደር ዋና** አስተዳዳሪ ነው።

2. ከንቲባው **ለከተማ አስተዳደር** ምክር ቤትና ለዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪ ሆኖ፦

ሀ) **የከተማ አስተዳደርን** ይወክላል፣

ለ) **የከተማ አስተዳደር** ምክር ቤትን ይመራል፤

ሐ) የፌደራሉንና የክልሉን ፖሊሲዎችና ህጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

መ) የከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት፣ ሌሎች ልዩ ልዩ ተቋማትና በስሩ የሚገኙ ክፍለ ከተማዎችን፣ ቀበሌዎችንና ሌሎች በከተማው ውስጥ የሚገኙ መዋቅሮችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ሠ) **የከተማ አስተዳደር** ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና ዕቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል፣ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

ረ) **የከተማ አስተዳደር** ነዋሪ ህዝብ ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ህግና ስርዓትን እንዲያስከብር የተቋቋመውን የፖሊስ ኃይል በበላይነት ይመራል ፣ይቆጣጠራል፤

ሰ) **ለከተማ አስተዳደር** ምክር ቤት፤ለከተማ አስተዳደር ምክር ቤትና ለዞን ወይም ለልዩ ወረዳ አስተዳደር በየጊዜ ሪፖርት ያቀርባል፤

ሸ) **የከተማ አስተዳደር** ምክር ቤት አባላትን **ለከተማ አስተዳደር** ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማ፤

ቀ) **የከተማ አስተዳደርን** ምክር ቤት መስራች ጉባኤ ይጠራል፤

በ) በ**ከተማ አስተዳደር** ምክር ቤትና በዞን ወይም በልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራትያከናውናል።

አንቀጽ 116. ስለ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ ስልጣንና ተግባር

የከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ ተጠሪነቱ ለዋና ከንቲባና ለ**ከተማ አስተዳደር** ምክር ቤት ሆኖ፦

1. ከንቲባው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፤

2. **የከተማ አስተዳደር** አስፈጻሚ ምክር ቤትና ከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

3. የምክትል ከንቲባው የስልጣን ዘመን በአንድ የምርጫ ዘመን የተገደበ ነው።

ክፍል አራት

የቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀትና ስልጣን

አንቀጽ 117. የቀበሌ አስተዳደር አደራጃጀት

1.የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻ መንግስታዊ አስተዳደር እርከን ሲሆን ተጠሪነቱ እንደ አግባብነቱ ለታቀፈበት የልዩ ወረዳ፣የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ነው።

2. እያንዳንዱ ቀበሌ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦

ሀ. ምክር ቤት፣

ለ. የአስተዳደር ምክር ቤት።

ሐ. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

አንቀጽ 118.የቀበሌ ምክር ቤት

1) የቀበሌ ምክርቤት የቀበሌው ነዋሪ ህዝብ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ ተቋቁሟል፤

2) የቀበሌ ምክርቤት አባላት በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ህዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ፤ ተጠሪነታቸውም ለመረጣቸው ህዝብ ነው።

አንቀጽ 119.የቀበሌ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የቀበሌ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የበላይ የሆኑት የመንግስት አካላት ከሚያወጧቸው ፖሊሲዎችና ህጎች ጋር በማይቃረን መንገድ በቀበሌው የውስጥ የአሰራር መመሪያ ያወጣል፤

2. ከምክር ቤት አባላት መካከል የቀበሌዉን አፈ-ጉባኤ፣ምክትል አፈ-ጉባኤ እና ዋና አስተዳዳሪ በምርጫ ይሰይማል፤

3. በቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ተመርጦ የሚቀርብለትን የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ሹመት ያጸድቃል፤

4. የበላይ በሆኑ የመንግስት አካላት የሚሰጡትን የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ እቅዶችንና ፕሮግራሞችን ተቀብሎ በቀበሌዉ ዉስጥ በስራ ላይ ያውላል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

5. የቀበሌው ነዋሪ ህዝብ ሰላምና ደህንነት መጠበቁንና ህግና ስርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፤

6. የተፈጥሮ ሀብትና ልማት እንክብካቤ ሥራ ይከታተላል፤

7. የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪንና ሌሎች የቀበሌው ባለስልጣናትን አሰራራቸዉን ይመረምራል፣ የሥራ መመሪያ ይሰጣል፣ ከኃላፊነትም ሊያነሳ ይችላል።

አንቀጽ 120.የቀበሌ ምክር ቤት አመራር

1. የቀበሌምክርቤት ከአባላቱ መካከል በቀጥታበሚመረጡ አፈ ጉባዔ እና ምክትል አፈ ጉባዔ ይመራል፤

2. በዚህ ሕገ መንግስት ስለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት አፈ-ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት ለቀበሌ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
3. ምክትል አፈ-ጉባዔው በአፈ-ጉባዔው ተለይቶ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤አፈ-ጉባዔው በማይገኝበት ወይም ስራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
4. በአፈ-ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 121. የቀበሌ ምክር ቤት ስብሰባ ጊዜ፣የሥራ ዘመንና ተጠሪነት

1. መደበኛ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያደርጋል፤ከምክር ቤቱ አባላት ሀምሳ ሲደመር አንድ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤
2. የምክር ቤቱ ዉሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙ የምክር ቤት አባላት በአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል፤
3. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤
4. ምክር ቤት መደበኛ ስብሳባ በማያደረግበት ወቅት አፈ-ጉባዔዉ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤
5. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ-ጉባኤዉ ስብሳባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 122. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት

1. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪና በቀበሌዉ ምክር ቤት በተጨማሪ ተመርጠዉ የሚሰየሙ የማህበራዊ እና አገልግሎት ሰጪ የመንግስት ተቋማት ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት ነው፤

2. የቀበሌ አስፈጻሚ ምክር ቤት በበላይ አካላት የሚወጡ ህጎችን የሚያስፈጽም የመጨረሻዉ አካል ይሆናል፤

3. የቀበሌ አስፈጻሚ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌዉ ዋና አስተዳዳሪ፣ ለቀበሌዉ ምክር ቤት እና እንደሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት የበላይ አስተዳደር እርከን ይሆናል፤

4. የቀበሌዉ አስፈጻሚ ምክር ቤት አባላት በተናጠልና በጋራ የቀበሌዉን አስተዳደር ሥራ ይመራሉ፣ያስተባብራሉ፤

5. የቀበሌዉ አስፈጻሚ ምክር ቤት አባላት ለሚያሳልፉት ዉሳኔ እና ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለባቸው።

አንቀጽ 123. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 120 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌውአስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የቀበሌው ምክር ቤት የሚያወጣቸውን የልማት እቅዶችን፤ ፕሮግራሞችን በሥራ ላይ ያውላል፤ ለ) የልማት እቅዶችን ይነድፋል፣ ለቀበሌው ምክር ቤት እያቀረበ ያስፀድቃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ) በቀበሌው ውስጥ የሚካሄዱ የማህበራዊ አገልግሎት እቅዶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤

መ) የቀበሌው ነዋሪ ህዝብ ሰላምና ደህንነት እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

ሠ) የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንክብካቤና የልማት ሥራ በከፍተኛ ደረጃ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ ህዝቡን ለልማት ሥራ ያነሳሳል፤ያስተባብራል፤

ረ) በአካባቢ ለሚገኙት ቅርሳ ቅርስ ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል፤ በጥቅም ላይ ስለሚውሉበት መንገድ የበላይ ለሆኑት አካላት ያሳውቃል፤

ሰ) በቀበሌው ምክር ቤት እና የበላይ የመንግስት አካላት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

2. የቀበሌ አስፈጻሚ ምክር ቤት የሥራ እቅዶችን የሚነድፈው፣ አፈፃፀማቸውን የሚከታተለውና የሚገመግመው በየጊዜው እየተገናኘ ይሆናል።

3. የቀበሌ አስተዳደር ጽህፈት ቤት የአስተዳደር ምክር ቤቱ እና የምክር ቤቱ ሥራዎች በጣምራ የሚከናወኑበት ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤ሆኖም እያንዳንዱ የየራሳቸውን ሥራ በየራሳቸው ቢሮ ያከናውናሉ፤

አንቀጽ 124. የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና የስልጣን ዘመን

1. **ዋና አስተዳደሪው በቀበሌው ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ከምክር ቤት አባላት መካከል በወረዳ ምክር ቤት ይሰየማል፤**

2. የዋና አስተዳዳሪው የስልጣን ዘመን በአምስት ዓመት የተገደበ ነው።

አንቀጽ 125. የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌዉ ምክር ቤት፣ ቀበሌው ለታቀፈበት የበላይ አስተዳደር እርከን ዋና አስተዳዳሪ ወይም ከንቲባ ሆኖ የቀበሌ አስተዳዳሪና የሥራ መሪ ነዉ፤

2. የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የቀበሌውን አስተዳደር ምክር ቤት ይሰበስባል ይመራል፤

ለ) የበላይ በሆኑት የመንግሥት አካላት የሚወጡትን ፖሊሲዎች፣ ህጎች እና እቅዶችን በሥራ ላይ ያውላል፤ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤

ሐ) ለቀበሌዉ አስተዳደር ምክር ቤት፣ ለቀበሌ ምክር ቤት፣ ለነዋሪዉ ህዝብና ለተደራጀበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር በየጊዜዉ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፤

መ) የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን እና ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ለቀበሌው ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል፤

ሠ) የቀበሌዉን ምክር ቤት መስራች ጉባኤ ይጠራል፤

ረ) በቀበሌው ምክር ቤትና በሚመለከተዉ የበላይ አስተዳደር እርከን የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል።

አንቀጽ 126. የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር፣የስልጣን ዘመን

ምክትል አስተዳዳሪው በዋና አስተዳዳሪው አቅራቢነት በቀበሌ ምክር ቤት የሚሾምና ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪና ለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሆኖ፦

1. ዋና አስተዳዳሪ በማይኖርበት ወይም ሥራዉን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

2. በቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤትና በቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ተለይተዉ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል፤

3. የምክትል አስተዳዳሪውየስልጣን ዘመን በአምስት ዓመት የተገደበ ነው።

ምዕራፍ አስር

የክልሉ መንግስት ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች

አንቀጽ 127.ዓላማዎችና መርሆዎች

ማንኛውም አካል ሕገ መንግስቱን፣ሌሎች ህጎችንና ፖሊሲዎችን በሥራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ የተመለከቱ መርሆችና ዓላማዎች ላይ መመስረት አለበት፤

አንቀጽ 128. ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች

1. መንግስት በዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት የክልሉ ህዝብ በሁሉም ደረጃ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን እና የዜጎች ተሳትፎ የሚረጋገጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፤

2. የክልሉ መንግስት የፈጣን ልማትን ራዕይ እውን ለማድረግ ከሙስና የፀዳ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልፅነት ያለው፣ለህዝብና ለሕግ ተጠያቂ በሆነ መልካም አስተዳደር መመስረት አለበት፤

3. የክልሉ መንግስት የብሔሮች፣ብሔረሰቦች እ ህዝቦችን ማንነት የማክበርና የማስከበር፣ በመካከላችው ሰላምን የማረጋገጥ፣ እኩልነትን፣ አንድነትን እና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት፤

4. የክልሉ መንግስት በልማትና በፖለቲካ ተሳትፎ ወደ ኋላ ለቀሩ ማህበረሰቦች ልዩ ድጋፍ በማድረግ እኩልነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፤

5. የክልሉ መንግስት ክልሉ ለማስተዳደር ሚያመች መልኩ ስልጣን ተዋረድ ላሉ የመ ግስት አካላት የማከፋፈል ግዴታ አለ ት፤

6. በዚህ ሕገ መ ግስት መሰረት የክልሉ መ ግስት የት ውም ደረጃ ክልሉን የማስተዳደር ሥልጣን አለው፤

7. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን ጉዳዮች አስመልክቶ ዝርዝር ህግ ይወጣል።

አንቀጽ 129. ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግስት ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ባላቸው እውቀትና ሀብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት፤

2. የክልሉ ኢኮኖሚ በዋናነት የተመሰረተዉ በግብርናና በእንስሳት ሀብት ልማት ላይ በመሆኑ መንግስት ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችንና እቅዶችን ሲቀርፅ የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት እና የኑሮ ደረጃውን ማሻሻል ማዕከል ባደረገ መልኩ መስራት አለበት፤

3. የክልሉ ሥነ-ምህዳር ሰፊ፣ በተፈጥሮ ሃብትና ጸጋ የበለፀገ በመሆኑ የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ ካለው እምቅ ሀ ት በፍትሐዊነት፣ በዘላቂነትና በእኩል ተጠቃሚነት የሚበለፅጉበትን እና ሀገር በቀል የግል ባለሀብቶች የሚፈሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፤

4. የክልሉ መንግስት ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ያላቸዉ የከተማ ነዋሪዎች እና የመንግስት ሠራተኞች በከተማ መኖሪያ እና የንግድ ቦታ እንዲያገኙ ያመቻቻል፤

5. የክልሉ መንግስት በልማት ወደኋላ ለቀሩ አካባቢዎች ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፤

6. የክልሉ መንግስት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከል፣ አደጋዉ ሲደርስ ለተጎጂዎች ሰብአዊ እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ የማድረግ እና በዘላቂነት መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፤

7. የክልሉ መንግስት የልማት ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ሲዘጋጁ፣ ሲተገበሩና ሲገመገሙ የህዝቡን ተሳትፎ ማረጋገጥ፣የኢኮኖሚና የልማት እንቅስቃሴዎችን መደገፍ አለበት፤

8. የክልሉ መንግስት የህዝቡን ዕወቀት፣ ጉልበትና ገንዘብ በማቀናጀት ፈጣን ልማትና እድገት የሚረጋገጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት፤

9. የክልሉ መንግስት በኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ሴቶችና ወንዶች እንዲሁም አካል ጉዳተኞች እኩል የሚሳተፉበትንና የሚጠቀሙበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት፤

10. የክልሉ መንግስት የህዝብና የሰራተኛውን ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅና ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለበት፤

11. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን ጉዳዮች አስመልክቶ ዝርዝር ህግ ይወጣል።

አንቀጽ 130.ማህበራዊ ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የትምህርት፣የጤና ፣የንጹህ ውሃ አገልግሎት፣የመኖሪያ ቤት እና የማህበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው ያደርጋል፤

2. የክልሉ መንግስት ነዋሪዎች ለሴቶች፣፣ለህጻናት፣ለአካል ጉዳተኞች፣ለአረጋዊያን እና ለልማትና የአካባቢ ጥበቃ ድጋፍ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራን ያበረታታል፤ይመራል፤

3. መደበኛ የመንግስት ትምህርት ሥርዓት ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶችና ከባህላዊ ተጽዕኖዎች ነጻ በሆነ መንገድ ይካሄዳል፤

4. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን ጉዳዮች አስመልክቶ ዝርዝር ህግ ይወጣል።

አንቀጽ 131. ባህል ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግስት መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን እና ነጻነቶችን፣ ሰብአዊ ክብርን እንዲሁም ዲሞክራሲንና ሕገ መንግስቱን የማይቃረኑ ባህሎችንና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤

2. የተፈጥሮ ሀብቶችን እና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ እና መንከባከብየመንግስትና የሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ግዴታ ነዉ፤

3. የክልሉ መ ግስት እ የክልሉ ነዋሪዎች ወጣቱን ትውልድ የመ ከ ከ፣ ተ ላ ሥ -ምግ ርና ስብእና የማ ፣ አካልም ሆ አዕምሮ ጠ ክሮ ላፊ ት የሚ ከም፣ ሀገሩ ና ወገኑን የሚወድ፣ የሚቆረቆር፣ ቁ ራሱ የሚተማመ ዜጋ ሆ እ ዲያድግ ከፍተኛ ጥረት የማድረግኃላፊነት አለ ቸው፤

4. የክልሉ መንግስት የክልሉን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ባህል፣ ቋንቋና ታሪካዊ ቅርሶችን በእኩልነት ለማሳደግና ለማዳበር ልዩ ትኩረት በመስጠት ተቋማዊ እንቅስቃሴ ማድረግ አለበት፤

5. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን ጉዳዮች አስመልክቶ ዝርዝር ህግ ይወጣል።

አንቀጽ 132. የሰው ሀብት ልማት እና የቴክኖሎጂ ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን ሥነ-ጥበብን፣ ኪነ-ጥበብን፣ ምርምር፣ጥናትን፣ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋትና በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች በፍትሀዊነት ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ ሃላፊነት አለበት፤

2. የክልሉ መንግስት ሥነ-ጥበብን፣ኪነ-ጥበብን፣ምርምርና ጥናትን፣ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የሚያስችል ዕዉቀት፣ ክህሎትና መሰረተ ልማት በፍትሀዊነት የማዳበርና የማጎልበት ሃላፊነት አለበት፤

3. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን ጉዳዮች አስመልክቶ ዝርዝር ህግ ይወጣል።

አንቀጽ 133. የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

1. መንግስት ሁሉም የክልሉ ነዋሪ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረዉ ከፍተኛ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤

2. ማንኛዉም የኢኮኖሚያዊ ልማት እርምጃ የአካባቢዉንና የነዋሪዎችን ደህንነት የማይጎዳ መሆን አለበት፤

3. መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኘዉ የአከባቢ ተፅእኖ ምዘና፣ ቁጥጥር እርምት የማድረግ ወይም የማስደረግ ግዴታ አለበት፤

4. መንግስት አካባቢ ደህንነት ጥበቃና ክትትል ህዝብ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ ማበረታታት አለበት፤

5. የክልሉ መንግስት የአካባቢ ደህንነትን የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራሞችን በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚያዉልበት ጊዜ የሚመለከተዉ ህዝብ ሀሳቡን እንዲገልጽ መደረግ አለበት፤

6. የክልሉ መንግስትና ነዋሪዎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ እና የመጠበቅ ግደታ አለባቸው፤

7. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን ጉዳዮች አስመልክቶ ዝርዝር ህግ ይወጣል።

አንቀጽ 134. የመሬትና ተፈጥሮ ሀብት ነክ ዓላማዎች

1. መሬትና ተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች ማህበራዊ ላፊነት ሚወጣ መልኩ መሆን አለባቸው፤

2. የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምን በተመለከተ ጥናት ላይ በተመሠረተ፣ የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነትን በሚያረጋግጥ፣ በተፈጥሮ ሀብት፣ በሰውናእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት በማያስከትሉ፣ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተስማሚ የሆኑግብርና ቴክኖሎጂዎችንና የግብዓት አቅርቦት ሥርዓት መከተል አለበት፤

3. ማንኛቸውም በመሬትና በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚካሄዱ የግብርናና የኢንዱስትሪ ልማት ፕሮግራሞች እንዲሁም ሌሎች ልማቶች መሬትንና ሌሎች ተያያዥ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃንና ከብክለን በተከተለ፣ የአካባቢና የአየር ንብረት ብክለትን በማያስከትልና በጥናት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ መካሄድ አለበት፤

4. የክልሉ መንግስት አገር በቀል የእጽዋትና የሰብል ዝርያዎችን በመሰብሰብ፣ በመንከባከብ እና በምርምር በማሻሻል ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ አለበት፤

5. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን ጉዳዮች አስመልክቶ ዝርዝር ህግ ይወጣል።

ምዕራፍ አስራ አንድ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 135. ስለ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

1. በፌዴራሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) እና በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 71 ንዑስ አንቀፅ 7 መሠረት ማናቸዉም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አዉጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤

2. በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 17 መሰረት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ባወጣበት በአስራ አምስት ቀናት ዉስጥ አፈ-ጉባኤው የክልሉን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ማሳወቅና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ ማስፀደቅ አለበት፤ አዋጁ በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለትሶስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ካላገኘ ወዲያውኑ ይሻራል፤

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣዉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለዉ ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል፤ ሆኖም የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ሲወስን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በየአራት ወሩ እንዲታደስ ለማድረግ ይችላል፤

4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስር የሚያወጣቸዉ ድንጋጌዎችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች በማናቸዉም ሁኔታ በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 17፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (1)(2)(3)(4)፣ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (4) (9) (11)፣አንቀጽ 22 ንኡስ አንቀጽ (2) (4) (5) (9) (10)፣ አንቀጽ 23 (1)፣ አንቀጽ 24፣ አንቀጽ 25፣ አንቀጽ 26 ንኡስ አንቀጽ (1) (3)፣አንቀጽ 30፣ አንቀጽ 37 ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) (ለ) (ሸ)፣(7)፣ (8) እና በአንቀጽ 38 ስር የተደነገጉትን መብቶች ተግባራዊነት የሚገድብ ወይም የሚያግድ መሆን የለበትም።

አንቀጽ 136. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ

1. በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአባላቱ ሦስት እና ከህግ ባለሙያዎች አራት መርጦ የሚመድባቸው በአጠቃላይ ሰባት አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ ያቋቁማል፤

2. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖሩታል፦

ሀ) በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት የታሰሩትን ግለሰቦች በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ይፋ ማድረግና የታሰሩበትን ምክንያት መግለፅ፣

ለ) በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የሚወሰዱ እርምጃዎች አስፈላጊ፣ ህጋዊና ተመጣጣኝ መሆናቸውን፣ የማይጣሱ መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶች ያልተጣሱ መሆኑን እና በማናቸውም ረገድኢ-ሰብአዊ አለመሆናቸውን መቆጣጠርና መከታተል፣

ሐ) ማናቸዉም የተወሰደ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃ ኢ-ሰብአዊ መሆኑንና አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን፣ መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶችንና ነጻነቶችን እና ሕገ መንግስቱን የጣሰ መሆኑን ሲያምንበት ርዕሰመስተዳድሩ ወይም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤቱ እርምጃውን ወይም አተገባበሩን በአፋጣኝእንዲያስተካክል ሀሳብ መስጠት፣

መ) በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃዎች ኢ-ሰብአዊ ድርጊት የፈፀሙ አካላት ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግና መብታቸው አላግባብ የተጣሰባቸው ሰዎች ተገቢውን ካሳ ስለሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት፣

ሠ) የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲቀጥል ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለውንአሰተያየት ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ ማቅረብ።

አንቀጽ 137. ስለ ክልሉ ዋና ኦዲተር መቋቋምና ስልጣን

1.የክልሉን መንግስት ተቋማትን እና የክልሉን የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ሂሳብ የሚመረምር፣ የሚከታተል፣ የሚቆጣጠር እና እንደአስፈላጊነቱ በኦዲት ግኝት ላይ ክስ ለሚመሰርት አካል ጉዳዩን የሚያቀርብ የክልሉ ዋና ኦዲተር በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፤

2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉ መንግስት ተቋማት እና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት ውጤት በተመለከተ ለክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ለተመርማሪው ተቋም ሪፖርት ያደረጋል፤

3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቀርቦ ያስጸድቃል፣ያስተዳድራል፤

4. የክልሉ ዋና ኦዲተር ተጠሪነቱ ለክልሉ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፤

5. የክልሉ ዋና ኦዲተር ዝርዝር ስልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።

አንቀጽ 138. የሕገ መንግስት ማሻሻያ ሀሳብ ስለማመንጨት

የሕገ መንግስት ማሻሻያ ሃሳብ፦

1. በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ሲደገፍ፤ወይም

2. በክልሉ የብሔረሰቦች ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ሲደገፍ፤ ወይም

3. በክልሉ ከሚገኙት የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች ውስጥ ሁለት ሦስተኛው በአብላጫ ድምጽ የደገፈው ከሆነ ለመላው የክልሉ ህዝብና የሕገ መንግሥቱ መሻሻል የሀሳብ ይዘት ለሚመለከታቸው ክፍሎች ለጠይይትና ለጠሳኔ ይቀርባል፤

4. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አካል የዚህ ሕገ መንግስት ማሻሻያ ሃሳብ ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በየደረጃው ለሚገኙ ምክር ቤቶች ሊያቀርብ ይችላል።

አንቀጽ 139. ሕገ መንግስቱን ስለማሻሻል

1.በዚህ ሕገ መንግስት ምዕራፍ ሁለት እና ሦስት፣ይህ አንቀጽ፣እንዲሁም አንቀጽ 139 ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል፦

ሀ) ሁሉም የዞን እና የልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በድምፅ ብልጫ ሲያጸድቁት፣

ለ) የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቀው፣ እና

ሐ) የክልሉ የብሄረሰቦች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ማሻሻያውን ሲያጸድቀው ነው።

2. በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በዚህ ሕገ መንግስት ምዕራፍ ሦስት የተዘረዘሩት መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች እና ነፃነቶች እንዲጸብሩና አዎንታዊ ይዘት እንዲኖራቸው ከሆነ የሚሻሻለው የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት በጋራ ሰብሰባ የቀረበው ማሻሻያ በአብላጫ ድምጽ ሲያጸድቁት ይሆናል፤

3. በንዑስ አንቀጽ 1 ስር ከተመለከቱት ውጭ ያሉት የዚህ ህገ መንግስት ድንጋጌዎች የሚሻሻሉት፦

ሀ) የክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት በጋራ ሰብሰባ በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ሲያጸድቁት፣ እና

ለ) በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት የዞን እና የልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች ውስጥ ሁለት ሶስተኛው የቀረበውን ማሻሻያ ሃሳብ ሲያፀድቁት ነው።

አንቀጽ 140. የተሻሩ ህጎች

1. የተሸሻለዉ የ 1994 የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ህገ መንግስት ተሽሯል።
2. ንኡስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ህገ-መንግስት ሲጸድ አስቀድሞ በህደት ላይ የነበሩ ጉዳይ በተሸሻለዉ 1994 ህገ-መንግስት መሰረት ይጠናቀቃሉ።

አንቀጽ 141.የመጨረሻ ህጋዊ ዕዉቅና ያለው ቅጅ

የዚህ ሕገ መንግሥት የአማርኛ ቅጂ የመጨረሻዉ ሕጋዊ ሰነድ ነው።